ሰሌዳ


ዲጂታል መጽሔት

ቅጽ ፩፡ ቁጥር ፩

ቃለአብ
ሚሊየን
ቤዛዊት
መስዑድ
ብሥራት

መጋቢት
2016 ዓ.ም

ሔሳዊ መጣጥፍ | ወግ | ልብወለድ |
ሽርሽር | ፌርማታ | እንቆቅልሽ |
ግብዣ | አርኬ



ቀዳሚ ቃል

መዲና ቃሉ በብዙ ሊተረጎም ይችላል። መደነ ከሚለው ግስ ይመዘዛል የሚሉ አሉ። መደነ አስተማረ፣ አሰለጠነ፣ ሥርዓት አስያዘ ማለት ነው። ዘመረ፣ አንጎራጎረ፣ አለቀሰ፣ ሙሾ አወረደ፣ ተቀኘ ማለትም ይሆናል። በዚህም መዲናን ደስታ ተከለ ወልድ ሲተረጉሙት "ብዙ ጊዜ ይዘቱ ሐዘንና እንጉርጉሮ የሆነ ባለ አራት መስመር የግጥም አይነት" ይሉታል። መዲና ከግጥም ቤቶች አንዱ ብቻ ሳይሆን ግጥሙ የሚዜምበት የመሰንቆ ጨዋታውም መጠሪያ ነው። መዲናና ዘለሰኛ እንዲሉ። በሌላም በኩል መዲና ነብዩ መሐመድ(ሰ.ዐ.ወ) በሒጅራ ጉዟቸው ከመካ ተነስተው የሔዱባት ከተማ ናት። ከነብዩ ሞት በኋላ ስሟ ወደ አል መዲና አል ሙነውራህ / AL-MADINAH AL-MUNAWWARAH እንደተቀየረ ይወሳል። የበራላት/ የበራችው ከተማ እንደማለት ነው። በኋላ ሲናበብ መዲና የሚለው ብቻ ቀርቷል። ከተማ ማለት ነው። በእስልምና ከመካ ቀጥሎ ሁለተኛዋ ቅድስት ከተማ ናት፣ መዲና። ይህንን ይዞ አማርኛው ዋና ከተማን መዲና ይለዋል። መናኸርያ፣ መሰብሰቢያ፣ ማእከል እንደማለት ነው።

መዲና በየወሩ የምትወጣ ኪናዊ መጽሔት ናት። በዚህኛው ምዕራፍ አስር ቅጾችን አካትታለች። ይኸ የመጀመርያው ቅጽ ነው። ዓላማዋ ስለሥነ ጽሑፍ እና ስለ ሌሎች የጥበብ ዘውጎች የምንወያይበትን አውድ ማስፋት፣ ወዲያውም ለአዳዲስ ፀሐፍት እና ለሥነ ጽሑፍ ነክ ውይይቶች መታያ ቦታ መፍጠር፣ ለተደራሲያኑም አማራጭ ጣዕም መስጠት ነው። ይህችንም መጽሔት የጥበብ ሰዎች መቀኛ፣ የጥበብ ወዳጆችም መናኸርያ ትኾን ዘንድ የሩቅ ሐሳብ አለንና መዲና ብለናታል።

“እናቴንማ ወዳጄን
አርግጥ ታለሁ ፈንታዬን
ገብታ በሆዴ ትብላላለች
የችግር ቀ/ቅኔ ትሆናለች።



ጋዜጠኛ - አቶ ለማ
ጋሽ ለማ ገብረ ሕይወት - አቤት
ጋዜጠኛ - መዲና እና ዘለሰኛ... ምን ማለት ነው?
ጋሽ ለማ ገብረ ሕይወት - መዲና ማለት ፈጣሪውን አመሰገነ ማለት ነው። ዘለሰኛ ለዓለማዊ ሆኖ ለጦር አለቆች ቅስቀሳ የሚሆን ነው።
ጋዜጠኛ - መዲና እንግዲህ... ተቀኘ ለማለት ነው።
ጋሽ ለማ ገብረ ሕይወት - አዎ... ተቀኘ ነው።
ጋዜጠኛ - እህ... እ... ከድሮ መዲና እና ዘለሰኛ ተጫዋቾች የታወቁት እነማን እነማን ነበሩ?
ጋሽ ለማ ገብረ ሕይወት - እኔ በማውቃቸው፤ ቀደም ያሉ ሊኖሩ ይችላሉ፤ እኔ ማውቃቸው ድረስ ያሉ...አቶ ይመር ተፈሪ የሚባሉ ነበሩ። ...እ... ወዳጆ ጌታሁን፤ ወርቁ መንገሻ፤ ዘገየ ካሣ፤ አሰፋ አባተ፤ አሰፋ ኃይሌ፤ አማረ ታየ፤ ተሾመ ሃብተ ማርያም... እነዚህ እነዚህ በሃገር ፍቅር ውስጥ ጥሩ መዳኝ የነበሩ ናቸው መዲና እና ዘለሰኛ።”
...
(ቆየት ካለ የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ቃለ መጠይቅ የተወሰደ)







ቅጽ 1፡ ቁጥር 1







ማውጫ

ፍሪዳ ካህሎ - FRIDA KAHLO 04
ሚሊየን

ሁሉም ነገር ተቀይሯል 08
ቢዛዊት

ሁለት ጥል 11
ሚሊየን

ዳዳ ግጥም 12
ብሥራት

የረከሰ ቤተ-መቅደስ 17
ቃለአብ

አንበሳ ማይመስለው አንበሳ 21
ብሥራት

አታምኑም እንዴ? 22
መስዑድ

ሥነግጥም | ግብጣ | እንቆቅልሽ

እፍታ



> *My painting carries with it the message of pain.*

ፍሪዳ ካህሎ- FRIDA KAHLO

አርቲስቱ ከአርቱ ይበልጣል?' ብለን እንድንጠይቅ ያስቻለን የአርቲስት ፍሪዳን ሕይወት እና ሥራዎች ማወቃችን ይኾን? የቱ ይበልጣል? ሠሪው? ወይስ ሥራው?

ፍሪዳ ካህሎ እኤአ በሐምሌ 9- 1907፣ በወቅቱ ከዋና ከተማው ትንሽ ራቅ ብሎ በሚገኝ ኮዮአካን የተባለ ሥፍራ ተወለደች። አባቷ የጀርመን አይሁድ፣ እናቷ የስፓኝ እና ሂንዲ ቅልቅል ነበሩ። ከተወለደች በኋላ እናቷ በመታመሟ፣ ጡት የምታጠባት ሠራተኛ ተቀጥሮላትም ነበር።

የስድስት ዓመት ልጅ እያለች በፖሊዮ በመጠቃቷ ለዘጠኝ ወራት ያህል ተሽሽጋ እንድትቆይ ኾነ። ያኔ ነው ለመጀመሪያ ጊዜ ምናባዊ ነገሮችን መሞከር የጀመረችው (በአካል የራቂት ህያው የዕድሜ እኩዮቿን የምትተካ የምናብ ጓደኛም ጭምር)። ከፎቶግራፈር አባቷ ጋርም ይበልጥ ተቀራረበች። ተሽሏት ከቤት ስትወጣ፣ እግሯ በመስለሉ፣ በእኩዮቿ ከመሰደብ አልተረፈችም። በስድባቸው እጅግ ብትበሳጭምና እርግማንን ብታዘንብባቸውም፣ ሦስት አራት ካልሲ ደራርባ መጫወቷን ግን አልተወችውም።

አልፎ አልፎ ከአባቷ ጋርም በሚሰራበት ቦታ ሁሉ አብራው ትሄድ ነበር። የሚጥል በሽታ ነበረበትና በሚወድቅ ጊዜ ካሜራው እንዳይሰረቅ ትጠብቃለች። ወደስቱዲዮአቸው ሲመለሱ፣ ትንንሽ የስዕል ብሩሾችን እየተጠቀመች ፎቶግራፎቹ ላይ መሳል ትለማመድ ነበር።

"There have been two great accidents in my life. One was the trolley, and the other was Diego. Diego was by far the worst. በሕይወቴ ኹለት ታላላቅ አደጋዎች ገጥመውኛል። አንዱ ባቡሩ ነው፣ ሁለተኛውና እጅግ የከፋው ደ'ሞ ዲዮጎ።"

ባቡር እና ዲዮጎ

በሜክሲኮ ሲቲ አለ የተባለ መሰናዶ ትምህርት ቤት ተቀላቀለች። ጓደኞቿም እራሳቸውን 'ካኩቾ' ብለው የሚጠሩ ነበሩ። በወቅቱ ታዋቂ ሰዓሊ እና ሴት አውል የነበረው ዲዮጎ ሪቬራ የትምህርት ቤታቸውን የአምፊቴአትር ግድግዳ እየሳለ ነበር። ለስዕል የሚጠቀምባቸውን ሞዴል ሴቶች ብዙ ጊዜ እርቃናቸውን ነበሩ። እና ስዕሉን ስሎ ከጨረሰ በኋላ ከሴቶቹ ጋር እዚያው 'ይተኛ' ነበር። እርሷ ይህንን ድርጊቱን በጊዜው ፍቅረኛዋ ከነበረው አሌሃንድሮ ጎሜዝ አሪያስ ጋር ኾና ተደብቃ ትመለከት ነበር። አንድ ቀን ግን አላስቻላትም "Panzon! Lupe is coming" ብላ ትጮኻለች (ቦርጫሙ! ሉፔ መጣችልህ!) ሉፔ ሁለተኛ ሚስቱ ነበረች። ሴት አውልም ቢሆን ፍሪዳ ካኩቾን ሳትመኘው አትቀርም። ለካኩቾ ጓደኞቿ "ከዚህ ሰውዬ ልጅ እንዲኖረኝ ነው የምፈልገው" ብላ ስትነግራቸው፣ በጣሙን ተገርመው ነበር።

ሜዲሲን ለመማር በወጠነችበት ጊዜ፡ አንድ ቀን ከፍቅረኛዋ አሌሃንድሮ ጋር ወደቤት እየተመለሱ ሳለ የተሳፈሩበት መኪና ከከተማ የኤሌክትሪክ ባቡር ጋር ተጋጭቶ አይሆኑ ጉዳት ተጎዳች። እግሯ፡ ቅልጥሟ (11 ቦታ)፡ ህብረሰረሰሯ (3 ቦታ)፡ የጎድን አጥንቷ (2 ቦታ) ስብራትን አስተናገዱ። ከሁሉም የከፋው እጅ መደገፊያ ብረት ዳሌዋን በስቶ በብሽሽቷ መውጣቱ ነበር። (ድንግልናዬን የወሰደው ብረቱ ነው ትል ነበር።)

ትተርፋለች' ብሎ ያሰበ ማንም አልነበረም። ለመከራ የፈጠራት ፍሪዳ ግን ተረፈች። መትረፏ ከዕድሜ ልክ ስቃይ ጋር ቢኾንም ቅሉ። ለወራት በ-Corset ታሽጋ፡ አልጋዋ ላይ ብትውልም። እናቷ አልጋዋ ላይ ኾና ስዕል የምትስልበትን ሲያዘጋጁላት አባቷ ደ'ሞ ቀለሞቹን ሰጠ። ፍሪዳ ይህን ጊዜ ስታስታውስ " ሕክምና መማር አልፈልግም እንጂ፡ ምንም ነገር ቢሆን ለመሥራት አቅሙ እንደነበረኝ ይሰማኛል። ስዕል መሳል ስጀምርም ለውሳኔ ብዙም አልተቸገርኩበትም። "

ካገገመች በኋላ የሳለቻቸውን ስዕሎች ይዛ ወደታዋቂው ሰዓሊ ዲዬጎ ሄደች። አንድ መርጣ ካስቀመጠች በኋላ፡ ከወደደው ቤቷ መጥቶ እንደሚጎበኛት ነገራት። በእርግጥም የሳለችውን ስዕል ወደደው። በዚያም ተቀራረቡ። መቀራረባቸው እስከጋብቻ የሚደርስም ኾነ። እዚህ ጋር እናት እና አባት ለሁለት ተከፈሉ። አባት፡ ለልጁ መታከሚያ ገንዘብ አጥሮታልና፡ ዲዮጎ ያን መሸፈን ይችላል ሲል ፈቀደ። እናት፡ 'ሴት አውል ነው፡ አይሆናትም' ብላ ቅር ተሰኘች። በመጨረሻም ተጋቡ


ትዳራቸው ግን ያን ያህል አልነበረም። ዲዬጎ ሌሎች ሴቶች ጋር መሄዱን አልተወም። ሴቶቹም እንዲሁ በቀላሉ ይሸነፉለት ነበር። ከሁሉም ከሁሉም የጎዳት ከታናሽ እህቷ ክርስቲና ጋር መውጣቱን ስታውቅ ነው። *The Two Fridas, Self Portrait with cropped hair,* እና *Memory The heart* የተሰኙ ሥራዎቿ መጎዳቷን የገለጸችባቸው ናቸው።

ስዕሎቿ አፍ አላቸው፡ ይናገራሉ። ሕመምን ያስተጋባሉ። ስለ ፍቺ (*The Two Fridas, Self Portrait with cropped hair,* እና *Memory The heart*)፡ መኪና አደጋ (*The bus, The broken Column*) ፡ ወንጀል (*A few small nips*)፡ መውለድ አለመቻልና ፍላጎት (*Roots, The wounded deer, My Grandparents My parents and Me*)፡ ውርጃ (*Henry Ford Hospital*)፡ የሳለቻቸው ሁሉ ለተመልካች በቀላሉ ይደርሳሉ። የሕይወት ታሪኳን የጻፈችው Hayden Herriera የፍሪዳን ካህሎ የስዕል አቅም/ፈጠራ ስትገልጽ "Pain Propelled Creativity" ነው ትላለች።

ከዲዬጎ ጋር አሜሪካ እየኖረች ሳለ እጅግ የምትጓጓለትን ልጅ በማጎጸኗ ተሸክማ ነበር። ለልጆች (እናት ለመኾን) ያላት ፍቅር ልዩ ነበር። ምን ያደርጋል! ውርጃ አጋጠማት። ወደ Henry Ford ሆስፒታል ስትወሰድ ደም እየፈሰሳት ሁላ ነበር። ከ13 ቀናት ህክምና በኋላ ወደቤቷ ስትመለስ የገጠማት ከባድ ድብርት ነበር። ያን ድብርት ለመታገል ስትል ሕመሞቿን አንድ በአንድ መሳሏን ቀጠለች።









The Broken Column


Henry Ford Hospital


Self Portrait with Cropped Hair

በእርግጥም ከዚያ ወዲያ የሳለቻቸው ስዕሎች ነበሩ ሕመማቸው ተመልካች ዘንድ በቀላሉ የደረሰው።

"I paint myself because I am so often alone, because I am the subject I know best."

ከመቶ በላይ ስዕሎቿ 55 የሚደርሱት የራሷን ምስል የያዙ (Self-portraits) ናቸው። ብቻዋን አሳልፋለችና፣ የምታውቀውም ራሷን ነውና፣ ያን ለመሳል በቅታለች።

"Be affectionate with Frida. She does not have children and she loves you very much."

ልጆችን ትወዳለች። የራሷም ልጅ እንዲኖራት አጥብቃ ትፈልግ ነበር። ውርጃ ልጅ እንዳይኖራት እደረጋት እንጂ። ቢሆንም መሻቷን ከመፈጸም ወደኋላ አላለችም። ለልጅ የነበራትን ፍቅር ለምታፈቅረው ዲዮጎ እንዲሁም ዲዮጎ ከሉፔ ለወለዳቸው ልጆች አሸጋገረች። እንስሳት የነበራትም ፍቅር ሳይጠቀስ የሚታለፍ አይደለም። ድመት፣ ጦጣ፣ በቀቀን፣ እርግብ፣ ንሥር እንዲሁም አጋዘን ቤቷ ውስጥ የነበሩ እንስሳት ናቸው፣ እንደ ልጅ ምትክ የምታያቸው። እነዚህንም *The wounded deer, Me and My parrots, Fulang Chang and I* በተሰኙ ሥራዎቿ ውስጥ አስገብታቸዋለች።

"Feet, what do I need them for if I have wings to fly?
እግር ሆይ! ክንፍ ስላለኝ አታስፈልገኝም።"

በልጅነቷ ፖሊዮ ያሰለለው፣ በወጣትነቷ 11 ቦታ ስብራትን ያስተናገደው ቀኝ እግሯ፣ እኤአ 1953 በጉልምስና እድሜዋ ጋንግሪን ተብሎ ከጉልበቷ በታች ተቆረጠ። ለመከራ የፈጠራት ፍሪዳ! አልጋ ቁራኛ ለመሆን የዳረጋት ገጠመኝ ነበር። በሕመም ማስታገሻ ደረጃ፣ ከባድ የሚባሉ ሕመሞችን የሚያስታግሰው 'ፔቲዲን' የተባለ መድኃኒትን አብዝታ ትጠቀም ነበር። አስቀድሞ ከዓመታት በፊት በፈረንሳይ የተደረገላት የስዕል ኤግዚቢሽን በሀገሯም ሜክሲኮ እንደሚደረግ ታወቀ። ዶክተሮች ግን የእርሷን መገኘት ተቃወሙ (ከጤናሽ ጋር አይሄድም በሚል)። ፍሪዳን ግን ያስቆማታል? አልጋዋን ሰዎች ተሸክመውላት የስዕል ኤግዚቢሽን የተዘጋጀበት ቦታ ተገኘች። ደማቅ ነበር የተደረገላት አቀባበል።

መውጫ

ፍሪዳ ካህሎ የሞተችበት ምክንያት ተደርጎ የሚወሰደው ለህመም ማስታገሻነት የምትወስደውን ፔቲዲን የተባለ መድኃኒት ከመጠን በላይ ወስዳ ነው ተብሎ ይገመታል። በዚህ ሰዓት ተወልዳ ያደገችበት እና ኋላም የሞተችበት ቤት ሥራዎቿን የያዘ ሙዚየም ሆኖ በአድናቂዎቿ ይጎበኛል። ስታይን ኖራ፣ ስታይን ስላ ያለፈችው ፍሪዳ ሥራዎቿ ዛሬም ድረስ ተወዳጅነታቸው እንደተጠበቀ ነው። እርሷ ባለችው አባባል ብንሰናበትስ?

"I leave you my portrait so that you will have my presence all the days and nights that I am away from you."

ልብሽ ላይ... ልብሽ ላይ ልሙት!

እንቺ የማርያም ሽቱ ብልቃጥ፣
ከንፈር ይሁዳሽ ይካደኝ፣
"እውነት ግን እውነት ምንድናት?"
ጲላጦስ ዓይንሽ ይፍረደኝ።
"ተግታችሁ ጸልዩ!" ብሏል፣
ጌቴሴማን ደረትሽ ላይ፣ መጸለይ መልስ ባያሰጥም፣
ጌታውም ታስሮ ተሰቅሏል፣
ከፍቅር መስቀል ሞት ጽዋ፣ እኔም ባርያው አላመልጥም።
ሰይፍ መምዘዝ መሰንዘሬን፣ ቆርጬ ዳግም መፈወሴን፣
ሞት መጥቶ ስሜን ሲጠራ፣ አቤት ብዬ መመለሴን፣
ተጭለምልመሽ በመስለምለምሽ፣ ላ'ንቺ ስል እሳት መልበሴን፣
ታያለሽ አለኳኮሴን!
ጣት እስኪላጥ እንጨት ልገው፣
ባልጩት ደንጊያ ፈትገው፣ የሚለኩሱት ተግ እንዲል፣
ታያለሽ የልቤን ቀንዲል፣
ለጌጥ ስደፋ 'ሾህ አክሊል፣
በፍቅር ጅራፍ ሊል ቀሊል፣
የመስቀልሽም ሸክም ጋብ ሲል።
ሳዶር አላዶር እዳው ገብስ፣
በመውደድ ላቆሰሉት ነፍስ፣
ታያለሽ... ጊዜዬ ሲደርስ።
ከእቅፍሽ መሰውያ መንበር፣ ከገነትሽ የሰላም ደጅ፣
ሆምጣጤሽም ያስተፈሰህ፣ መጻጻም ሐሞት ወይን ጠጅ።
ደም ወማዩን ሊያንቆረቁር፣ ለንጊኖስ ጦሩን በገቦው፣
የእግዜርን ዓይን ሊደነቁር፣ የአይሁድም ሽንገላ በአግቦው፣
ከመስቀሉ ፊት ታድሞ፣
ከዙፋኔ ግርጌ ቆሞ፣
ታያለሽ... ታያለሽ ደግሞ!
***
ታዲያ ምነው ባትጨክኚ፣ ነፍስያሽ ነፍሴን ባይበድል፣
ቀራንዮ ልቡናሽ ላይ፣ ምናል ሞቴን ባደላድል?
ኤሎሄዬም እንኳ መከኖ፣ ምሕረትሽን ከበከለ፣
መውደድሽ እንደስብከቱ፣ ፍቅርን ኖሮ ካላከለ፣
ወርጂልሽ ሰው መሆኔ፣ ምልክናሽን ከከለለ፣
እጅ እግሮቼን መቸንከሬ፣ መብረርሽን ከከለከለ፣
ሞት ጽዋሽ አላልፈኝ ካለ፣
የምሰዋበትን ቦታ እንኳ...ጎልጎታዬን ብመርጥ ምናለ?
እዚያው ልብሽ ላይ...

ልብሽ ላይ ልሙት!

ለገብረ ክርስቶስ ደስታ



ሁሉም ነገር ተቀይሯል

ደራሲ | ቤዛዊት

(....)

ሁሉም ነገር ተቀይሯል-

እንደ አስማት፣ እንደ ምትሀት እንደ ተዓምር ነገር ተመልሶ በእጅ ላይጨበጥ - ተመልሶ በትር ላይሆን ... አሁን የነበረ የለም! የተረፈችው ይህቺ ቁር ያቆፈደዳት አውላላ ሜዳ ላይ ብቻዋን የተከዘች ደሳሳ ጎጆ ናት> የሷ ጉልበት ካበጃጃት ብርቱ ክንድ በምን ስልተ-ምት ከፈጣሪዋ ገዝፋ ለዛሬ እንደታጨች ሚስጥር ነው። የሆነችውን ሆናም እወዳት አለሁ> .. ትዝታዬ እሷ ውስጥ ሲሆን ስጋና ደም ይለብሳል፣ ሲንቀሳቀስ አየዋለሁ፣ ድምፁ ይሰማኛል፣ የሚያወጋጋኝ የቀረልኝ እሱ ነው። ... ከሷ ባሻገር ያለውን ዓለም እጠላዋለሁ! ከጉበኔ ማለፍን እፈራለሁ! ከሷ አልፎ የሚያጓጓኝ የለም።

በማለዳ ደጃፌን ስከፍት የበሩን ቁመና ይዛ ግድግዳው ላይ ለምትሰጣው የማለዳ ጀንበር በእጄ ዓይኔን ከልዬ የማሽኮረምምላት፣ የምሰጣት ፊት የለኝም። በሬን ስከፍት የሚጠብቀኝ የማውቀው መንደር አይደለም። በማለዳ ጥሩንባ የሚነፉት፣ ‘‘እከሌ ሞተን’’ የሚለፍፉት ጋሽ ጀምበሬ የሉም። "ደህና አደራችሁ ወይ?" የሚል የመንገደኛ ድምፅ አይሠማም። በደጄ የሚያልፍ ሰው የለም። እንደመርዶ ነጋሪ በሌሊት እቃ ለመዋስ በሬን እየቆረቆረች ሳይነጋ ክፉ ደግ የምታናግረኝ ብዙዬም የለችም። ለቡና ጠጡልኝ ቀድሞ ጉብሉን የሚልክ ቡና አጣጭ፣ ነገሬን አማካሪ፣ ሮሮዬን ሰሚ ወዳጅ የለኝም።

በሬን ስከፍት እየተንጫጩ የሚቀበሉኝ እነዛ መልከኛ ወፎች እንኳን ቁራን ሽሽት ዛሬ ከጎጇቸው ተሰደዋል። ሁሉም የአቅሙን ጓዙን ሸክፎ ሲሄድ እንጀቴን አስሬ፣ ተሰናብቼ በዓይኔ ሸኝቼ ተለይቻቸዋለሁ። የምለማመነው ጌታ የለኝ። የአልነጃሺ በር ተሰብሯል፣ አጥቢያ ደብሬ ነድዷል፣ ማዘኔን የማዋያቸው በመስቀላቸው ሚደባብሱኝ ቁስ ታምሬ የሉም። - ጋጣዬ ውስጥ የሚያናፋ አህያ፣ የሚያስገመግም ፈረስ የለም። እነ ጥላዬ ስንት ዘመን ሞፈር ተሸክመው፣ አፈር ገፍተው፣ እህል የሠፈሩበትን ቦታ ጣጥለው ሄደዋል። በረቱ ባዶ ነው። እህል ጭቃ የሆነባት፣ ደግሺ ያበላሁባት፣ ስንቁን የዳርኩ፣ የኳልኩባት፣ ሀይሎጋ የተረገጠባት፣ አቧራው የጨሰባት መንደሬ ዛሬ የደም መሬት ሆናለች - አኪልዳማ... !

ይህ ሁሉ የሆነው እንደ ህልም እንደ ቅዠት ድንገት ነበር። ዓለምዬ የአረጋዊ ወዳጅ ነውና የዓመቱ አረጋዊ ሲሆን ለፀበልተኛው የሽንብራ ቆሎ እና በሶ ይዘን ከዓመት እንዴ የመሄድ ልምድ ነበረን። ለጉዞ እየተሰነዳዳን ያዘጋጀሁትን ሽንብራ እና በሶ በቅጥ በቅጡ ሳደርግ ነበር የተኩስ ድምፅ መሰማት የጀመረው። የሰፈሩ ሰው በየስፍራው እሪታውን ያቀልጠው ጀመር፣ ነገር ሁሉ ትርምስምሱ ወጣ።

ዓለምዬ የደመ ነፍሱን "አባዬ አባዬ" እያለ ወደ ቦኖ ውኃ ልትቀዳ የወረደች የልጃችንን ስም እየጠራ ሲሮጥ የያዝኩትን ሽንብራ የሞላ ሰፈድ በቁሜ ለቀቅሁት። ተከትዬው ልሩጥ ብል እግሬ በጀ የሚል አልነበረም። ጋቢውን እያውለበለበ ሲከንፍ ባለሁበት በድኜ ከዕይታዬ እስኪሰወር ድረስ በዓይኔ ተከተልኩት። ወደ’ኔ አቅጣጫ የሚሮጠው የ’ሷ ታላቅ ጎትቶ ወደቤት እያስገባ

“አይዞሽ እታለም፣ ደኅና ይመጣሉ። አይዞሽ ምንም አትሆንም” ሲለኝ ልቤ ግን አውቆት ነበር።

እንደማይሆን ባውቀውም ጠብቄያለሁ፣ የእናት አንጀቱ ሆዴ እየነገረኝ ጠብቄያለሁ። ዓመታት የሚመስሉ ሰዓታትን በተስፋ ጠብቄያለሁ። መጠበቅ ህመም ነው፣ መጠበቅ በሽታ ነው! በዚህ ላስታግስህ የማይሉት በሽታ ... ሆኖም እጠብቃለሁ! ግን እግራስ ያለ እመሉ መች ጠፋው? ለምልከት አይደል? እባ አንጀቱ ስር ተቋጥሮ የቀረ ስጋዋ ላይ ያለ ነገር መች ተንሰፈሰፍኩ? እወቂው ሲለኝ አይደል? አዎ እናትነቴ ቀድሞ ነግሮኝ ነበር።

... ዓለምዬ ከሩቅ ብቅ ሲል ሳየው ግን ድጋሚ ተስፋ አድርጌ ጠብቄያለሁ። አበባዬን ከጀርባው ወይ ከጎኑ ላያት ተመኝቼ ነበር። ያገኘኋት የታጠፉ እጆቹ ላይ... ወደሆዱ አስጠግቶ እጅና እግሯ ግራና ቀኝ እየተንዘላዘለ፣ አንገቷ ወደ ኋላ አዘንብሎ አገጯ ወደሰማይ አንጋጦ... እቅፉ ስር ነበር። መጥቶ የተደፋሁበት መሬት ላይ በጉልበቱ ወደቀ። አጠገቤ ደርሶ እጄ ስር እስካገኛት ደግሜ ቀና ልል አቅም አልነበረኝም። "ቀጠፉብኝ አበባዬን ቀጠፉብኝ " ይላል ሲያወራ ከአፉ ደም ፍንጥቅ ይላል። በጉልበቱ ተንበርክኬ ዝቅ ብዬ አየኋት፣ እንደ ቀልድ የለችም። ሳላውቀው፣ ሳይነግረኝ፣ ሳልጠረጥር እንደ ቀልድ ሄዳለች፣ እንደ ቀልድ ወስዷታል።

ግን እንደ መስጠት ሁሉ ለመንሳትስ ሂደት አያስፈልግም ነበር? ዘጠኝ ወር የማየት ጉጉት ለመንሳት ሲሆን አይሰራም? ሹሩባ ልሠራ ያስተካከልኩት ይኼ የተመሳቀለ ጸጉሯ ስንት ቀንና ሌሊቱን ፈጅቷል? ስንት ዓመት ቃላትን ያላመድኩት፣ ዓመት ሁለት ዓመት ለመጠራት የጠበቅሁት፣ ያ እንደበቷ ድንገት እንዲህ እንዲዘጋ ነበር? ጭኔ ላይ ተኝታ፣ ዓይኔ ላይ የምታንከባለለቻቸው እነዚያ ዓይኖቿ ጸጉሯን ሳልደባብስላት እንዲሁ ዝም ብለው ያለ ልምዳቸው መከደን ነበረባቸው? ግን ተከደኑ፡፡ ቁንጥጫዬን ያላየው ያ የሳሳሁለት የሞላ ጉንጯ በሰንበር ተሞልቶ የጭኗ ስጋ በጥይት ተቦትርፎ አጥንቱ ገጦ ቀሚሷ በደም ተነክሮ፣ እንደታረደ በግ ሆና ከእንገቷ ስር ደሟ እየጎረፈ፣ ልጄ ዓለሜዋ ገላዋን ቀድሜ እንዳየሁት ከሆዴ ስትወጣ እንደነበረው በደም ተለውሶ ጉልበቱ ስር፣ እቅፌ ላይ አገኘኋት። አንጀቱ ተቆረጠ!!

ከእጄ የበሉት የአደዬ ልጆች ቀን አታለላቸው፣ ስጋቸውን በሉ። የእህቱን ደም እመልሳለሁ ብሎ የአባቱን ምንሽር ታጥቆ ለዝክር ከተባለ በሶ በጀርባው አንግቶ ታላቋ ዘመተ። ለንግሱ ስሄድ ቤት ለእዝጊሃር ብላ እግሬን በሙቅ ውሃ አጥባ ጥሀሎዋን ሰርታ እንባሻዋን ጋግራ የተቀበለችኝ አደዬም ደግሞ ልታነባ ልመናዬን ረግጦ ሄደ። እንግዲህ ምን እንበል የዘራነው ፍቅር ፍሬውን አርግፎ እሾህን ሲያበቅል እኛም አላየንም፣ እኛም አላመንንም።

አበባዬን ከቀበርኩ ኋላ ሰው ሁሉ ጓዙን እየሸከፈ ከብቱን እየነዳ የኖረበትን፣ ተዛምዶ የተጋመደበትን፣ አብሮ ክፉ ደግ ያሳለፈበትን ቀዬ ወደ ኋላው ትቶ ጉዞውን ሲጀምር የዓለምዬ ወዳጅ አያ በልስቲ መጥቶ "ውባለም፣ ዓለማየሁ ደህና አይመስለኝም። ጓዝሽን አሰናጅና በጊዜ አብረን እንሂድ፣ ከኋላ ቀርቶ ያስቸግርሻል" ሲለኝ ልብ ብዬ ዓለምዬን እየሁት፣ የኔ ብርቱ! ያ ጀግና ገበሬ፣ የከብቶቹ ጌታ አዕምሮውን ስቷል። አባትነቱ ወንድነቱን የልጁን ክብር ዓይኑ እያየ በግፍ ሲነጠቅ በስስቱ በትንሿ ልጁ ደም ተለክፎ እንዳይሆን ሆኗል።

ሲለው ይወራጫል ሲለውም ይጮኻል፣ ሮጦ ያመልጠው ይመስል ይሮጣል፣ የጠራው ወይ ብሎት ላይመጣ ይጣራል፣ ያለ ነገር ይወራጫል፣ መሬት ይጭራል። አልሆን ሲል እጁ በሰንሰለት ተጠፈረ። ይገርመው አልሰደድ፣ ትቼው አልሄድ የቸገረ ሆነ። ቢጠሩት “ወይ” አይል፣ ቢነኩት አይሰማ፣ እንደው ፍዝዝ ይላል። ... የቤቴን ጌታ መመኪያ ጋሻዬን እንደ ልጅ ተቆጣሁ፣ እንደ ህፃን አታለልኩት። ከዚህች ቤት ግን ወይ ውልፍት አለ። ሁሉም ሲሄድ ብቻችንን ቀረን። አብረን እንዳልኖርን እንደው እንደ እንግዳ በማላውቀው ዓይን ያየኛል፣ እንደ ባዳ ይሸሸኛል። ድንገት ደግሞ ሲጮህ በቁጣ ዓይን ሳየው እንደ ልጅ ይደነግጣል። በመደንገጡ እደነግጥና በራሴ አዝናለሁ አልቅሼ “ይቅር በለኝ” እላለሁ። "ይቅር በለኝ ጋሻዬ! ይቅር በለኝ ዋርካዬ! ምን ላርግ ዓለምዬ?! ምን ላርግ ዘንካታዬ?! ያኔደለን ቀን ነው! የጀገነው ጊዜ ነው! " ምን ብለፈልፍ እሱ ምን ተዳው? የጀመረው ሰሞን ቅዠትም ቢሆን ሳወራራው ይመልስልኝ ነበር።

ስንሰነባብት ግን ዝምታው አየለ፣ እጁ ላይ ስለታሰረው ሰንሰለት ግድ አይሰጠውም። ተደብቆ ሊፈታ ሊያታልለኝ አይሞክርም፣ እንደ ወትሮው አይነጫነጭም። እዛችው መደብ ላይ ተቀምጦ በተበሳሳው ጣራ አልፈው የሚገቡ ፍንጣቂ ጨረሮችን በእግሩ ሊሸፍን ይሞክራል። አንዱን መርጦ እግሩን ሲጭንባት እሱን አልፋ እግሩ ላይ ስትሆን ሌላኛውን እግሩን አንስቶ እግሩ ላይ ሲጭን እሁንም ከላይ ስትሆን በመሸነፍ አይነት ቀና ብሎ መምጫዋን አይቶ እግሩን ሰብስቦ እንደገና ይኮራመታል። ሊያየኝ አይፈልግም ፊቱን ወደ ግርግዳው ስር ቀብሮ ይደበታል። ሲጮህ እንዳልተቆጣው ዝም ሲል ይጨንቀኛል።

“ተው ዓለሜዋ! እብደትም ለዛ ያለው ሲጮሁበት ነው!” እለዋለሁ ድምፅም የለው - ዝም። እሱ ከዛኛው ጥግ ከመደቡ ላይ፣ እኔ እዚህ ምድጃዬ ስር ዱካዬ ላይ ተቀምጠን በመሀላችን በሚነደው የእሳት ብርሀን መሀል አልፈ አየዋለሁ። ድንገት ካየኝ ዓይኑን ይሰብራል። 'አዬ ዓለምዬ እንደው ፎጣውን እግርህን ብሸፍንበት... አመዱ ላይ ከምታንኮራትተው እግርህም እኮ ደነዘዘ " - ግንባሩን ኮሶ ያስመስለዋል “እንዳሻህ” ብዬ እተወዋለሁ። ከምሞቀው እሳት ተነስቼ በፊቱ እመላለሰላሁ፣ ጉዳዩ አይደለሁም። ሌሊት ተነስቶ እንዳይሄድ፣ መኝታዬን በሩ ስር አነጥፋለሁ፣ እያየኝም .. "ደህና እደር አለምዬ" -ዝም ...!!

ከምንጣፈ ላይ ተንጋልዬ ነገ ስለማበላው እህል አስባለሁ። ርጋፊ የጨፍ ዱቄት ለነገ ቂጣችን ብትሆን፣ ዛሬን ተስፋ ካሳደረን ከዛሬ ነገ ይበልጣል፣ ለነገ ስንቅ ብትሆነን ትንፋሽስ ቀለብ አይደል? ሁለት ቀን ብንዘል ከዛ ቤት ውስጥ የሚቀረው ለፀበልተኛ የተዘጋጀው የአረጋዊ በሶ ነው ... ዝክር እንዴት ሆኖ ይበላል? ... ስለት እንዴት ሆኖ ከጉሮሮ ይወርዳል? የታቦት ሀቅ እንዴት እሺ ብሎ ተሆድ ውስጥ ይገባል? እንዲህ ሳስብ ይነጋል ደግሞ .... ቀናት ሳምንታት ምናልባት ወራት ... ለምን ያህል ጊዜ ቤት ውስጥ እንደተዘጋን ሳላውቀው ጊዜው ሄደ። የመጣ የለም፣ የተመለሰ የለም። የሰው ወሬ የአእዋፍ ድምፅ የለም። ጫጫታው ወይወይታው ተኩሱ ሁሉ ካለፈ ሰነብቷል። አሁን ሁሉም ወና ነው።

.... "ውሀ ስጪኝ" ሲለኝ ቤት ውስጥ ብቻዬን ያለሁ ይመስል መለኮት እንዳናገረኝ ደንግጬ ተነሳሁ። በርግጥም መለኮቴ ነው፣ በርግጥም ብርሀኔ ነው፣ ይህ ድምፅ ተስፋዬ ነው። ማሰሮዬን ወደ ኩባያዬ ሳዘቀዝቅ ግን ውሃ አልነበራትም። ጋኑ፣ ማድጋው፣ ኩስኩስቱ፣ ደምበኛኑ ... ሁሉም ባዶ ነበር። "አሄሄ ተው ዓለምዬ! ተው! ይህቺን ታሪክ አበባዬ ከመጽሐፍ ላይ እንብባ ደጋግማ ነግራኛለች። እኔ ውባለም ነኝ፣ እንደ ውድነሽ በጣሙ አልታለልም። ትቼህ አልሄድም! ምን ባልወደው፣ ምን ብፈራው ከጉድጓዳችን ከተደበቅንበት አብረን ነው የምንወጣው።

አየሁት ዓይን ዓይኔን ያየኛል "ና እንሂድ ውሃ እንቅዳ" አፈፍ ብሎ ተነሳ። "ደጄ ምን ቢናፍቅህ ነው ዓለሜዋ?" ወደኔ ዞሮ ፈገግ አለለልኝ። የፈራሁትን ዓለም ደፈርኩት፣ ሳልደበቅ ፊቴን ለብርሀኑ ሰጥቼ በራፌን ከፈትኩ። የሰንሰለቱን ጫፍ ይዤ ከፊቱ ቀደምኩ ተከተለኝ። ማንም የለም፣ ምንም የለም። አልፎ አልፎ የደረቀ ደም እየረገጥን፣ ወደፊት ተራመድን። ወዳጁ ቤት ሲደርስ እንደመቆም አለና ጮክ ብሎ "እንዴት አደርክ በልስቲ?" አለና ወደእኔ ዞረ። እንደሱ ጮክ ብዬ "እንዴት አደራችሁ አስካለ?" አልኩ፣ የበልስቲ ባለቤት ናት ። ፊቱ ፈካ፣ ፈገገልኝ።

ድጋሚ መራመድ ጀ መ ር ን ...

ወደ ፊታችን....

ወደ ውኃችን ...



ፊርማታ

ኹለት ጸብ

እንደኛው

“ አባቱ ትናንት የደስ ደስ 200,000 ብር ለቀቀብኝ፤ እና ላካፍልህ ፈልጋለሁ፤ መቶ ሺ ብሩን ውሰድ የኔ ጌታ” አለችኝ።

ይኼን ሁላ ብር እንዴት ልትሰጠኝ ወደደች? ለአንድ ባጃጅ ሹፌር፤ ይህን ያህል ብር ሰጠችኝ ማለት እኮ ወር ሙሉ ሳልሰራ እየቃምሁ እረፍት ማድረጌ ነው። ነዳጅ ተወደደ አልተወደደ ሳልጨነቅ፤ ስለ መለዋወጫ ዋጋ ሳልጠበብ... ወር ሙሉ እረፍት። ግን ይህ ሁሉ ብር? እንዲሁ በቀላሉ ውሰድ? እንዴት ልትሰጠኝ አሰበች?

በእርግጥ ፍቅረኛሞች ከሆንን ወራት ቢቆጠሩም አባቷ ይህን ያህል ሀብት እንዴት እንዳመጣ፤ ደ’ሞ እንዴት ሊሰጣት ይችላል? ብዬ አሰብሁ። ሲጀመር አባቷን የት አውቀዋለሁ? መቼ ነገረችኝ?

“ ይህ ሁሉ ብር ከየት አምጥቶ ነው”
“ ሞኑን፤ በሁለት ቀን ውስጥ ብቻ 12 ሚሊዮን ብር ትርፍ ዘግቶ ነው”
“ በሁለት ቀን?”
“ እም! ጎበዝ ነጋዴ ነው”
“ ምንድነው ሥራው?”
“ ነዳጅ ማደያ አለው”

በነጋታው ተጣላን።

ኹለተኛው

እንደምትወደኝ አውቃለሁ፤ እንደምትፈልገኝ ግን ስላልነገረችኝ ሀሳቧ ምን እንደሆነ መገመት ይቸግረኛል። ቀጥታ መጠየቁ ደበረኝና፤

“ በህይወትሽ ምን ቢኖርሽ ትፈልጊያለሽ?” ብዬ መልዕክት ሰደድሁላት።
“ ዋናው ፍላጎቴ ሰላም ነው። (በእርግጥ ገንዘብም ያስፈልገኛል። ፍቅርንም እሻለሁ። አንተንም)

በነጋታው ተጣላን።

ማትስ አስተማሪ መሆኗ ነበር የጥላችን ምክንያት።

አጫሬፊራ

ዳዳ ግጥም (DADAISM)

በሃያኛው መቶክፍለ ዘመን ከተነሱ የሥነጥበብ ንቅናቄዎች መሀል ዋነኛው ሲሆን ከርሱ ቀጥለው በመጡት እንቅስቃሴዎች ላይ ተጽዕኖውን ያሳረፈ እንቅስቃሴ ነው።

ዳዳ አመክንዮ እና ተጠየቅ አይመቸውም። ከንቁ አእምሯችን የሚመጡትን ወይም ንቁው አእምሮ የሚረዳውን ቋንቋ አይመርጥም ከዛ ይልቅ ደመነፍስን ይመርጣል (ትከሻዬ ነገረኝ፡ እንዲሁ ታወቀኝ እንደምንለው የለም? እንደሱ)።

ይህ እንቅስቃሴ የተጀመረው ሁጎ ቦል (Hugo Ball) በ1916 ከአንደኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ነው። ዓላማውም ዘመናዊ ነኝ ያለውን ዓለም ማፈራርስና አዲስ ቅርጽ ለመስጠት መሞከር ነው። በዳዳ ስነግጥም የአዘቦቱን ቋንቋ በቃላት በመከፋፈል (በsyllables) እና እነዚህን ቃላት ቦታ በመቀያየር ቀድሞ የነበረውን ሰዋስው በማፍረስ አዲስ ትርጉም የሌለው ድምጾችን ይፈጥራል። በዚህም የአንደኛው ዓለም ጦርነት ያመጣውን መፈራረስ ፈክሮበታል። ሌላው የዳዳይዝም ሥነ ግጥም ቋንቋ ለታለመለት ዓላማ ታማኝ እንዳልሆነ ያምናል። ይህም ማለት የአንድ ነገር የቃል ውክልና ያንን ነገር የመተካት (represent የማድረግ) አቅሙ ውስን ነው። በነገርዬው እና በቋንቋው (ውክልናው) መሀል ምንም አይነት የስሜት ዝምድና የለውም። ይህንን ደግሞ ንቁ ባልሆነው አእምሯችን እና በስሜታችን ልንረዳው አይቻለንም በማለት ነው እንቅስቃሴውን የጀመረው።



ወቅቱ ኤግዚስተንሻሊዝም ጽንሰ ሀሳብ የመዘበት (Peak ላይ የደረሰበት) ዘመን ስለነበር ዳዳይዝም ላይ ተጽዕኖውን ማሳረፉ አልቀረም። ኤግዚስተንሻሊስቶች በዚህች ትርጉም በሌላት ወለፈንዲ ህይወት፡ ቋሚ እና ተፈጥሮአዊ የሆነ እውነት የለም የእነዚህ ሁሉ ነገሮች ግለሰባዊ አተረጓጎም (subjectivity) ነው ይላሉ። የዳዳይዝም ግጥም በዚህ subjective በሆነው ትርጉም እያንዳንዱ ግጥሙን የሚሰማው ሰው በራሱ አረዳድ ግጥሙን ተርጉሞ እንዲረዳው ይጋብዛል። ይህ የግጥም እንቅስቃሴ በደንብ ስሜት የሚሰጠው ገጣሚው በራሱ የድምጽ ከፍታ እና ዝቅታ ሲያነበው እንጂ በጽሁፍ ሲቀርብ አይደለም። ነገሩ ህይወት ራሱ መች ትርጉም አላትና?

በሰኔ 23 1916 ዓ.ም ሁጎ ቦል ጠንካራ፡ አብረቅራቂ ሰማያዊ ቀለም የተቀቡ ካርቶኖች እንደልብስ ለብሶ፡ ጨለማ በዋጠው የካብረት ቮልቴይር (Cabaret Voltaire) መድረክ ላይ የለበሰው ካርቶን እንደልቡ ስለማያንቀሳቅሰው በሰዎች እርዳታ ወጥቶ ቆመ። መድረኩ ላይ እንደጅብራ ተገትሮ በዝግታ መወጣት ጀመረ። በዘፈቀደ የተሰደሩትን ቃላት በቁም ነገር እና በአክብሮት ድምጹን ከፍ፡ ዝቅ እያደረገ ለተገኙት ታዳሚያን አቀረበላቸው። ያን ቀን ያቀረባቸው ግጥሞች Gadji beri bimba፡ Wolken (Labada's Song to the clouds) እና Karawane (Elephant Caravan) የተሰኙ ናቸው።



Karawane (excerpt)
ü üü ü
schampa wulla wussa olobo
hej tatta gorem
eschige zunbada
wulubu ssubudu uluwu ssubudu
tumba ba-umf
kusa gauma
ba - umf

የዳዳ ግጥሞች በሚታወቁና ትርጉም በሚሰጡ ቃላት አይዋቀሩም፡ ከዛ ይልቅ ቃላቱ በሚነበቡት ጊዜ፡ ቀራጺ ከአለት ተጠንቅቆ ቅርጹን እንደሚያወጣው ልክ እንደዛ የሚወጣው ድምጽ በጥንቃቄ የግጥሙን ስሜት ማጋባት አለበት። ሁጎ ቦል ግጥሙን፡ ሰማይ በከባድ ዝናም ምድሪቱን ሲያረሰርስ እንደሚያወጣው ያለ አስገምጋሚ ድምጽ፡ ወይም ጅብ ለድሪያ ሲሰናዳ የሚያሰማው ማሽካካት ያለ ቀፋፊ ድምጽ፡ ወይም ክርስቶስ በመስቀል ላይ <<ኤሎሄ ኤሎሄ ለማሰበቅታኒ>> ብሎ የጮኸውን አይነት ታላቅ ጩኸትን፡ ወይም እነዚህን ሶስቱን እያደረገ አንብቧቸው እንዳወጣጡ በሰዎች ታዝሎ ከመድረክ ወርዷል።
ሌላው እንደሁጎ ሁሉ የተለያዩ ሙከራዎችን ያደረገው ኩርት ሽዊተር (KURT SCHWITTERS) ለ40 ደቂቃ የረዘመ ursonate የተሰኘ ግጥም አቅርባል።

MOUVEMENT DADA



ከዚህ በታች በማስቀምጠው መመሪያ መሰረት አንድ የዳዳ ግጥም እንጽፋለን።

1. አንድ ጋዜጣ፣ ወይም የመጽሐፍ ገጽ፣ ወይም ጽሑፍ ያለበት ወረቀት፣ አንድ መቀስ፣ (የመጽሐፍ ወይም የጋዜጣ ወረቀት ለመቆራረጥ የሚከብዳችሁ ደግሞ እርሳስ እና ወረቀት ከመቀስ ጋር ማዘጋጀት)

2. ከጋዜጣ ወይም ከመጽሐፉ የወደዱትን አንዱን አንቀጽ ቆርጠው ያውጡ (አለቀድም ያሉ ወዳጃችን ጽሁፉን በያዙት ወረቀት ላይ ይገልብጡት)

3. ተቀድዶ የወጣውን አንቀጽ በታል ደረጃ ቆራርጠው ለየብቻ ያስቀምጡት።


4. የተቆረጡትን ቃላት በአንድ ላይ በቦርሳ ወይም በአንድ ዕቃ አድርገው ይጥውዙት እና አንድ በአንድ እያወጡ ይደርድሩት።

5. ሁሉንም ደርድረው ሲጨርሱ ግጥሙን ጮክ ብለው ያንብቡት!

6. ታድያ የጻፉትን ግጥም ለኛ መላክ እንዳይረሱ!

ሰናይ ጊዜ!

ድግስ



ነጋሪት ባንድ በ2012 ዓ.ም የተመሰረተ ባንድ ነው። ከዚህ በፊት በፈንድታ የባሕል ማእከል በሚያቀርቡት ሥራቸው እናውቃቸዋለን። በቅርቡ "Origins!" የተሰኘ የመጀመርያ አልበማቸውን አቅርበውልናል። ሐገርኛ የሆኑ ዜማዎች ቀርበውበታል። ጃዝ ኢትዮጵያዊ በሆነ መንገድ ተተርጉሟል። ለዚህ ባለሙያዎቹ ራሳቸው ያወጡት "Indigenous Jazz" የሚል ስም በደንብ ይገልጸዋል። ከአባውዴ ዝማሬ እስከ ያሬድ ዜማ፣ ከሰሜን ከደቡብ፣ ከምስራቅ ከምዕራብ ኢትዮጵያ ውስጥ አለ የተባለ ድምጽ ሁሉ የቀረ አይመስልም፣ ጃዝነቱ ሲፈተሽ። እኛ ወድደነዋል። ታዳምጡት ዘንድ ግብዣችን ነው።



የፌልም ግብዣ

Fig Tree (የሾላ ዛፍ) - ዓለም ወርቅ ዴቪዳን በልጅነቷ ኢትዮጵያን ለቅቃ ወደ እስራኤል ያደረገችውን ጉዞ መነሻ በማድረግ ጽፋ ያዘጋጀችው (direct) ፊልም ነው። ፊልሙ በ1982 ዓ.ም ሚና የምትባል የ16 ዓመት ልጃገረድ ፡ ፈላሻ እናቷን ተከትላ ወደ እስራኤል በመሄድ እና የወንድ ጓደኛዋ የሆነውን ኤሊ ትታ ባለመሄድ መሀል ስትዋልል ያሳያል። ፊልሙ በግዜው የነበረውን የሀገሪቷን ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ውጥረት በአንድ ቤተሰብ ላይ ተመስርቶ ለመዳሰስ ሞክሯል። ይህንን ፊልም ትመለከቱት ዘንድ መዲና ትጋብዛለች።





የመፅሐፍ ግብዣ

እሁንም እይደል ወደ ማታ - በሔኖክ ደመቀ በ2015 ዓ.ም የተጻፈ የአጫጭር ተረኮችና የግጥሞች ስብስብ ነው። በውስጡ ሃያ ተረኮችን እና ወደሠላሳ የሚጠጉ ግጥሞችን ይዟል። ታነብቡት ዘንድ ግብዣችን ነው።

አዘጋጅ | ቃለአብ ዓባይነህ

ሒሳዊ መጣጥፍ

የረከሰ ቤተ መቅደስ

(ጠብያ ግጥምን በጃዝ እንደማሳያ)

መቼ ለት ነው ገጣሚ መንበረ ማርያም ኃይሉ (የቃል ሰሌዳ) ቲክ ቶክ ላይ የግጥም ግብአተ መሬት እየተፈጸመ ነው ብላ በፌስቡክ ገጿ አርድታኝ ከቲክ ቶክ መንደር ብወርድ እውነትም የሥነግጥም ቀብር ላይ ደረስሁ። እዩዬም የለ! እልልም የለ! እንዲሁ ዓይን መጨፈንና ማነብነብ ብቻ። (የእንድ ደቂቃ የሕሊና ጸሎት የሚሏት ነገር ነበረች ድሮ። ማንም አጣርቶ አያውቅም እርሷ ነገር የምር እንድ ደቂቃ ትሁን አትሁን።) በወዲህ በኩል ደግሞ ጠብያ የግጥምን በጃዝ መድረካችን የልደት በዓሏን[1] በዚህ ወር ታከብራለች። በእኒህ ሁለት ነገሮች መነሻነት ስለሥነ ግጥምና ስለ ክዋኔው ጥቂት ብናወጋስ?

ግጥም እንደ ክውን ስንክን (Poetry as a Performed Art)

ግጥምን በሠፈው ብያኔው ብንወስደው ሊቀርብባቸው የሚችልባቸው ዐውዶች አራት ዓይነት ናቸው። እንደኛውና ጥንታዊው በቃል የሚቀርበው ሥነ-ቃላዊ ዐውድ ነው። በዚህ ዐውድ ውስጥ ግጥም የተመጠነ ዓላማ ይኖረዋል። ቀድሞ ስለማይጻፍና ስለማይጠና ግጥሙም ከዋኔውም ብዙ ጊዜ ድንገቴ ነው የሚሆነው። በዜማ፣ በውዝዋዜ አልያም በትወና ሊታጀብ ይችላል። ሙሾ ለዚህ አሪፍ ምሳሌ ነው። ይኼ ዐውድ በኋላ ከምናነሳው ቴክኖሎጂያዊ አብዮት ኪነ-ጥበብ ጥንቧን እንድትጥል ከማድረጉ ጋር ተያይዞ በዘመን ብርቱ ከንድ እየተገፋ በከተሜነት እየተገፈተረ እየራቀን እየራቀን እየጠፋ ነው። አሁን ሸገር ውስጥ አልቃሽ ፈልጎ ማግኘት ከባድ ሆኗል። አሁን ጎንደር ብትሔዱ ደንበኛ እዝማሪ ማግኘት የሚቻል አይደለም። ይኼንን ሥነ ቃላዊ ክዋኔ እያጣነው ይመስለኛል በግሌ።

ሁለተኛው ዐውድ ዕድሜ ለዮሐንስ ጉተንበርግና ለኢንዱስትሪ አብዮት ግጥሞች በአንድ ጥራዝ የሚታተሙበት፣ ለአንባቢም የሚደርሱበት ዐውድ ነው። ይኼ ከሥነ-ቃላዊው ዐውድ ቀጥሎ በጣም የዳበረው ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። ምንም እንኳ የግጥምን ክዋኔያዊ ባህርይ ቢያስቀርብንም በተለያየ ዘመንና ቦታ ላሉ አንባብያን የንባብ እና የክዋኔ ነጻነቱን፣ የመተርጎሙንም ሥልጣን (Power of Interpretation) ስለሚያጎናጽፍ ለዘመናት ገናና ሆኖ ነበር። እንደውም ከዘመነ ኢንተርኔት በፊት ሌሎቹን ቅርጾችና የአቀራረብ ዐውዶች በጅምላ ማምረት የሚችለው ቴክኖሎጂ በመስፋፋቱ (በተለይ የድምጽ መቅጃ እና የምስል መከሰቻ ሳጥኖች መፈልሰፍ) ወጀብ እንደናጣት ጀልባ ሲንኮታኮቱ በዚህ የአቀራረብ ዐውድ ላይ ግን በአሉታዊ መልኩ የጎላ ተጽዕኖ ሲያሳድሩበት አላየንም ነበር። በእስራ ዘጠኝ ዘጠናዎቹ መጨረሻና በአዲሱ ሚሊንየም መባቻ ላይ ተከስቶ የነበረውን የግጥም መጻሕፍት ህትመት ርካሽነት በተለይ በእንድ ሳምንት ሁለት ሦስት የግጥም መጽሐፍት ይወጡበት የነበረውን ዘመን ማስታወስ በቂ ነው። አሁን ከዲጂታል የንባብ መሳሪያዎች ቅለትና መስፋፋት ጋር በተያያዘ፣ በዓለም ሙቀት መጨመር እንዲሁም በወረቀት መወደድ ምክንያት የህትመቱ ነገር ልክ እንደሥነ-ቃሉ ሁሉ የጉብዝና ዘመኑን ጨርሶ መቃብር አፋፍ እንደቆመ ሆኖ ይታያል። ቤት ንብረታቸውን ሽጠው መጽሐፍ በሚያሳትሙ ጥቂት ጀብደኛ እና ደጋግ ሰዎች ትከሻ ላይ ተንጠልጥሎ የመንግስትንና የባለጸጎችን እርጥባን ይጠባበቃል። ይኼ በመጽሐፍት ጠረን ተከቦ ላደገ ሰው ሁሉ ከባድ መርዶ ይመስለኛል። ራሱን የቻለ ውይይትና ምክክርም ያሻዋል።

ሦስተኛው ዐውድ ገጣሚው ድምጹን አሰምቶ ግጥሙን የሚያነብበት ዐውድ ነው። ገጣሚው አእምሮው ውስጥ ያለ ድምጽ አለው፣ የሚመራበት። ምንም እንኳ ለሁሉም ገጣሚያን ይኼ ቀመር ይሰራል ባይባልም አብዛኞቹ ግን ያቺን ድምጽ፣ ዜማዋን፣ የልባቸውን ሥልተ ምት ተከትለው ነው የሚጽፏት። ስለዚህ አእምሮው ውስጥ ያለውን ለማውጣት ይሞክራል። አንዳንዴ አሪፍ የሚጽፉ ሰዎች ይኼ ዐውድ አይሆንላቸው ይሆናል። አንዳንዴ ደግሞ ውሽልሽል ግጥሞች በንባብ ብልሃት ድጋፍ ጣፋጭ መስለው ይታያሉ። ይህ ክዋኔ ከላይ ያነሳነው የህትመት ዐውድ የሚሰጠውን የንባብና የሙከራ ነጻነት ስለሚገፍ ተጽዕኖው ከባድ ነው። ‹እንደ እገሌ ማንበብ› ‹እንደ እገሊት ማንበብ› የሚባል ነገር የሚመጣው እዚህ ጋር ነው። ከላይ ያነሳነው ሁለተኛው ዐውድ ለብልህ አንባቢ ድምጹን አሰምቶ ማንበብ በመለማመድ ከገጣሚው ተጽዕኖ ውጭ የራሱን ድምጽ ለመፈለግ ያስችለዋል። ልክ ቴፕ ላይ የሬድዮ ጣብያ እንደሚፈልግ ሰው ድምጹን፣ ክዋኔውን እየለዋወጠ የራሱን የሚስማማውን ንባብ ያገኛል።

17 [1] ጽሑፉ ጦቢያ ግጥምን በጃዝ ልደታቸውን በሚያከብሩበት ሐምሌ ወር ላይ የተጻፈ መሆኑን ልብ ይሏል።

ይኼ ሦስተኛ ዐውድ ምንም እንኳ አንዳንዴ ወጣኒያንን እጅ ይዞ ለመምራት ቢረዳም በአንባቢው አእምሮ ውስጥ የገጣሚውን ድምጸት በማተሙ ምክንያት ለግጥም ከዋኔ ድግግሞሽንና ብልየትን ሊያመጣ ይችላል።

አራተኛውና ዘመነኛው፡ ዛሬም ልናነሳው የወደድነው ንኡስ ዐውድ ግጥም እንደ አንድ የኪነጥበብ ዘውግ ከሌሎች ቅርጾች ጋር እየተዛመደ (ከሙዚቃ፣ ከትወና እና ከውዝዋዜ ጋር ለምሳሌ) የሚቀርብበት ዐውድ ነው። በውጪው ዓለም ሲለማ Slam Poetry ሲከፋ ደግሞ Battle Rap እየተሰኘ ቅርጹ ዳብሯል። ከተለመዱት አላባዎች በተጨማሪ እንደ 'Delivery' ያሉ አላባዎችን ጨምሯል። ይኼ የመከወን ዐውድ በሥነ ግጥም ብቻ ሳይሆን በሌሎች የኪነጥበብ ዘውጎች ውስጥም አለ። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የአማርኛንም ሥነ ጽሑፍ እያጥለቀለቀው እና የወጣቱንም ትውልድ ትኩረት እየሳበ ይገኛል። ለዚህ ምክንያቱ ጠንካራና ዘላቂ፣ አማራጭ አልባ በሆነ ሁኔታ ወጣቱ በቀላሉ ሊያገኘው የሚችለው የኪነ ጥበብ መድረክ ጠቢያ ግጥምን በጃዝ ስለሆነ ነው። ይኼ ተጽዕኖው እንዲሁም በነጋ በጠባ ባንዶችና የኪነ ጥበብ ቡድኖች (የፖለቲካ ፓርቲዎችም ጭምር) እንደ እቃቃ ጨዋታ በሸ ብትን በሚፈርሱበት ሀገር ለዘመናት መዝለቁ መድረኩ ምን ያህል ጠንካራና ብርቱ በሆኑ ሰዎች እንደሚመራ ያሳያል። ይኼ ሊመሰገን የሚገባው ነገር ነው።

ነገር ግን ከሰሞኑ በግልጽም በድብቅም ማጉረምረሞች እየተሰሙ ነው። የጽሑፉ ዓላማ ስለነዚህ ማጉረምረሞች ጥርት ባለ መልኩ ማሰብ ነው። እነዚህን ማጉረምረሞች እንመርምር!

ማጉረምረም አንድ - ግጥም ራሱን ችሎ መቆም አለበት።

በብዙ መልኩ ስናየው ገጣሚ ልክ እንደ በገና ደርዳሪ ነው። በገና በመደርደር ማዜም የሚችል ሰው በገና መደርደር ከማይችል ሰው ለመለየት በጣም ይቀላል። እንግዲህ እንደምታውቁት በገና አስር አውታር አለው። ከአስሩ አውታር ብዙ ጊዜ አምስቱ ድምጽ የሚያወጡ ናቸው፣ አምስቱ ደግሞ ጣት ማሳረፊያ ይባላሉ። ቁምነገሩ ያለው ድምጽ ማውጣቱ ላይ አይደለም። ትርጉም የሚሰጥ ድምጽ ከማውጣቱ ላይ ነው። ድምጾቹን በሆነ ቅደም ተከተል መደርደር ደግሞ ትርጉም የማሸከሚያ አንዱ መንገድ ነው። በገና ደርዳሪን በገና መደርደር ከማይችል ሰው የሚለየው ይኼ ነው። በገና ደርዳሪ ዜማ ለመፍጠር ከየትኛው አውታር በኋላ የትኛውን መንካት እንዳለበት ያውቃል። ፒያኖ ተጫዋችም እንዲሁ ዜማ ለመፍጠር አንዳች ዓይነት ቅደም ተከተል ባለው መልኩ የፒያኖውን ቁልፎች መጫን አለበት። እንደኔ ያለው በገና መደርደርም ሆነ ፒያኖ መጫወት የማይችል ሰው የዜማ መሳርያዎቹ ቢሰጡት እንኳ ድምጽ ያወጣ ይሆናል እንጂ ዜማ አይፈጥርም። ገጣሚም ልክ እንዲሁ ባለአስር ሳይሆን የትየለሌ አውታሮች ባሉት በገና እንደሚያዜም ሰው ነው። ወላ አውታሮቹ እነሱኝ ካለ ምንም እንኳ ያሉት አውታሮች ራሱ የትየለሌ ቢሆኑም የፈለገውን ያህል አውታር ፈጥሮ መጨመር ይችላል። እኒህ አውታሮቹ ቃላት ይባላሉ።

ገጣሚ በቃላት ላይ ሥልጣን ያለው ሰው ነው። ቃላት በራሳቸው የድምጾች ጥርቅም ናቸውና የቱን ቃል ከየቱ አስከትሎ ቢያመጣው ዜማ መፍጠር እንደሚችል ያውቃል። እናም ቃላትን እየመረጠ በተመረጠ ቦታቸው ላይ ያስቀምጣቸዋል። እዚህ ጋር 'ግጥም ማለት የተመረጡ ቃላት በተመረጠ ቦታቸው ሲቀመጡ ማለት ነው።' ያለውን ሳሙኤል ታይለርን እናስታውሳለን። ተራው ሰው እንኳንስ ቃላቱን የሚያወጣበትን ቅደም ተከተል በማሰብ ቦታቸውን መምረጥ ቀርቶ ቃላቱን እንኳ መርጦ ለመናገር ግድ አይሰጠውም። ገጣሚ ግን የቃላት ጌታ ነውና እንኳን ስለቃላቱ ስለሚያርፉበት ቦታም ይገደዋል። ይጨነቃል! የት ባደርጋቸው ይሻላል ብሎ። ይኼ ደግሞ ግጥም መግጠምን ማደብና ጥሞናን ማካበት የሚጠይቅ የንቁው ሕሊና ተግባር (Conscious Act) ያደርገዋል። የግጥም የገጣሚም ልዕልና የሚመጣው እዚህ የንቃት ተግባር እመሆኑ ላይ ነው። ገጣሚው ምንም ይሁን ምን አውቆ ጠንቅቆ እንጂ ስቶ ዘንግቶ የሚያስገባው ነገር አይኖርም። ሰው ዜማ ለመፍጠር ድምጹን መጠቀም ይችላል፤ እንደበገና እና እንደፒያኖ ያሉ የዜማ መሳሪያዎችንም መጠቀም ይችላል። በእነዚህ መሳሪያዎች የሆኑ የሆኑ ድምጾችን አከታትሎ ሲያወጣ ዜማ ይፈጥራል። ገጣሚ ግን ለማዜም የሚጠቀመው ቃላትን ነው። እያወራ ያዜማል፤ ልክ እንደወፍ።

ከሙዚቃ ውጪ በእነዚህ ዘመነኛ መድረኮች ክዋኔ ላይ ግዙፍ ተጽዕኖ ያለው ትወና ነው። ከላይ ካነሳናቸው አራት የማቅረቢያ ስልቶች ውስጥ በሆነ መልኩ ትወናን የማያሳትፍ አቀራረብ ቢኖር ሁለተኛው የህትመት ዐውድ ብቻ ነው። እርሱም ቢሆን ከሙዚቃ እና ከሌሎች ክውን ጥበባት ጋር ባይዛመድም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ለስዕልና ለሌሎች የህትመት ጥበቦች ክፍት ሆኗል። ከእኛ ሃገር ከቆዩት የከበደች ተክለአብን እና የጋሽ እሸቱ ጥሩነህን "የት ነው?" የተሰኘው የከበደች ተክለ አብ መድብል ላይ መጣመር ማንሳት ይቻላል። ከቅርብ ጊዜዎቹም ከእኛው ሃገር የተሰፋሁን ከበደ 'የሞት ጥቁር ወተት' ከውጪ ደግሞ ሁለቱንም የሩፒ ካዉር (Rupi Kaur) መድብሎች ማየት በቂ ነው።

በበኩሌ ግጥምን በጃዝ ስንልም ሆነ ከሌሎች ከውን ጥበባት ጋር እዛምደን አዲስ የጥበብ ፈለግ እንፍጠር ስንል ልብ ልንላቸው የሚገቡ ሁለት ነገሮች አሉ ባይ ነኝ። አንደኛው ለጥበብ ፋይዳ አዲስ እሴት መጨመር ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ጥገኝነትን ማጥፋት ነው።

የኪነ ጥበብ በተለይ ደግሞ የሥነ ግጥም ፋይዳው ምንድን ነው? ነፍሱን ይማረውና ብርሃኑ ገበየሁ ‹የአማርኛ ሥነ ግጥም› በተሰኘ መጽሐፉ ቋንቋ ሁለት ፋይዳዎች አሉት ይለናል። አንደኛው ዘለለታዊው የማግባባት ፋይዳ ነው። ይኼ ተራው ህዝብ የሚጠቀምበት መደበኛ መረጃ የመለዋወጥ ግልጋሎት ነው። በቋንቋ መልዕክት የማስተላለፍ እና የማግባባት ብቃት ላይ የተመሰረተ ነው። ሁለተኛው ግን ከቋንቋ ብቃት ሳይሆን ድክመት የሚመነጨው ቅኔያዊ ፋይዳ ነው። ቋንቋ ያግባባል ብንልም ያለው እውነታ ግን እንደዚያ አይመስልም። በቋንቋ ልንገልጻቸው የማንችላቸው ነገሮች ይኖራሉ፤ አሉምም። ታላቁ አስትያዊ ገጣሚ ሬይነር ማርያ ሪልከ (Rainer Maria Rilke) ለአንድ ወጣኒ ገጣሚ የላካቸው ደብዳቤዎች ተሰብስበው በታተሙበት Letters to a Young Poet በተሰኘ ጠማሩ ተመሳሳይ ነገር ይነግረናል። *“Things aren’t all so tangible and sayable as people would usually have us believe; most experiences are unsayable, they happen in a space that no word has ever entered…”* ይላል። እውነቱን ይመስለኛል። ይህ የገባኝ የፍራንዝ ካፍካን “Letters to Milena” ሳነብ ነው። ብዙ ነገር ይላታል ካፍካ ለሚሌና። ብዙ የሚያማምር ነገር። ብዙ ፍቅር የሚያስዝ ነገር። ግን ሌላ ባል አላት እርሷ። ስለፍቅር ቢያወሩም አልተግባቡም። በመጨረሻ *“Milena, help me! Understand more than I am saying”* ይላታል። ላተናው ደራሲ የታላት ሃብታም ነው ሲባል ቋንቋ የሚባለው ነገር ራሱ ሽባ ይሆንበታል። ይላታል። *“I can not make you understand. I can not make anyone understand what is happening inside me. I can not even explain it to myself.”* Letters to Milena ይኼ የቋንቋ ሽባነት የተገለጸበት አሪፍ ስራ ነው። በዚህ የቋንቋ ሽባነት ሃሳብ ጂብራን ካህሊል ጂብራንም ሆነ ከላይ ያነሳነው ሬይነር ማርያ ሪልከ ይስማሙበታል። ሬይነር ማርያ ሪልከ ቀደም ሲል ባነሳነው መጽሐፉ ውስጥ *“… for ultimately, and precisely in the deepest and most important matters, we are unspeakably alone; and many things must happen, many things must go right, a whole constellation of events must be fulfilled, for one human being to successfully advise or help another.”* ይለናል። ጂብራንም *“Between what is said and not meant, and what is meant and not said, most of love is lost.”* ይላል። የነካፍካ ታሪክ የሚያሳየው ይኼንን ነው። መፍትሄው ጥበብ ነው ይለናል ጂብራን። ኪነጥበብ ካልነው በላይ እንድንል ያደርገናል። ያልን ከሚመስለው በላይ ሰዉ እንዲገባው ያደርጋል። በሥነ ጽሑፍ በተለይ በሥነ ግጥም ታላት ካላቸው መደበኛ ትርጉም ውጪ ብዙ ትርጉም እንዲሸከሙ ይሆናል። ይህን ሲገልጽ ጂብራን *“Wisdom is not in words; wisdom is meaning within words.”* ይላል። አንድ ሰው መጥቶ ለአራት ለአምስት ሠዓታት እናቱን ምን ያህል እንደሚወዳት ቢነግረን ለእናቱ ያለው ፍቅር የሚገባን ቀርቶ ታግሰን የምናዳምጠው ጥቂቶች ነን። ነገር ግን በሁለት መስመር ግጥም የእናቱ ፍቅር እንዲሰማን አድርጎ መሄድ ይችላል። ይኼ በሆነ መልኩ ምትሐታዊ የሆነው የኪነ ጥበብ ፋይዳ ነው፥ ቅኔያዊ ፋይዳ።

በአስራ ዘጠነኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጨረሻ ላይ ሰዓልያን በፎቶግራፍ ካሜራ መፈልሰፍ ምክንያት ከፊታቸው የተጋረጠው አደጋ በደንብ ታይቷቸው ነበር። መሰረታዊው ጥያቄ አንድ ባለሦስት አንጻር (3D) የሆነን አካል እንዴት ነው በባለሁለት አንጻር (2D) ወረቀት ላይ መወከል የምንችለው የሚለው ነበር። የፎቶግራፍ ካሜራ መምጣት ስዕልንና ሰዓሊያንን ከፍተኛ የትርጉም (Purpose) ማጣት ውስጥ ከቷቸዋል። ለዘመናት የሥነ ስዕል ጥበብ የተመሰረተው በዚህ እውነታን እንዳለች አድርጎ በማስቀመጥ ብልሃት (Realism) ላይ ነበር። በጣም እውነታውን የሚመስል ስዕል መሳል የሚችል ተማሪ ነው በብሉዩ የሥነ ስዕል ባህል ጎበዝ የሚሰኘው። በዚህ በአስራ ዘጠነኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጨረሻ አካባቢ ከካሜራ መፈልሰፍ ጋር አብረው የነበሩት እንደ ፓብሎ ፒካሶ እና ሄነሪ ማቲስ ያሉ ሰዓልያን ያደጉት በዚህ ብሉይ ባህል ነው። አሁን ግን ካሜራ መጣና ከእነርሱ በተሻለ ብቃት በፍጥነት፥ በርካሽ እና በጥቂት ድካም የሰዎችን እውነታ ቁጭ አድርጎ ማስቀረት አስቻለ። ይህም ለዘመናት የባለጸጎች ቡችላ ሆኖ የኖረውን ሥነ ስዕል ከእውነታዊነት (Realism) ነጻ አወጣው። ስለዚህ ሰዓሊያኑ አዲስ ትርጉም መፈለግ ጀመሩ። ምንድነው ስዕልን ከፎቶግራፍ የሚለየው? ቲያትርም ከፊልም ኢንዱስትሪው መምጣጥ በኋላ ተመሳሳይ የትርጉም ማጣት ቅርቃር ውስጥ ገብቶ ነበር። መፍትሄው ሁሉ የኪነጥበብ ዘርፍ እንደመሆናቸው መጠን እያንዳንዳቸው ከሌሎቹ በተለየ የሚጨምሩት ፋይዳ፥ ትርጉም ለማሸከም የተለያየ ቴክኒክ ተጠቅመው የሚጨምሩት የትርጉም ልባስ (Layer) መኖር እለበት የሚለው ነበር። ይህንን የተረዱት እነ ፒካሶ እና እነ ሄነሪ ማቲስ ሥነ ስዕልን ከገባበት ከትርጉም ማጣት አዘቅት ውስጥ ያልነውን የትርጉም ልባስ በመፍጠር ታደጉት። የሚታያቸውን ብቻ ሳይሆን ያይት ነገር እንዲሰማቸው ያደረጋቸውን ስሜት ጭምር መሳል ጀመሩ። በተለይ ፒካሶ ከዚህ አልፎ ኪዩቢዝም (Cubism) የተባለውን ስልት ፈጠረ።

ሃሳቡ ምንድነው? ፎቶ የሚያሳየው ፊት ለፊት የተሰጠውን ብቻ ነው። ለምሳሌ በነሞናሊዛ ዘመን ፎቶግራፍ ካሜራ ቢኖር የሚያነሳው ፎቶ አሁን እኛ ዳቪንቺ ስሎት ከምናየው ጋር ተመሳሳይ ነበር የሚሆነው። ነገር ግን የሞናሊዛ ፊት ባለሦስት አንጻር(3D) ነው። ፎቶውም ሆነ ብሉዩ ሥነ ስዕል ይህንን ማሳየት አይችሉም። ስለዚህ ፒካሶ መጣና ካሜራ ሊይዘው የማይቸለውን የፊቷን ባለሦስት አንጻራዊ ክፍል ሁሉ በባለሁለት አንጻር ሸራ ለማሳየት ሞከረ። ያንንም Cubism በማለት ሰየመው። ፎቶግራፍ ማድረግ የማይችለውንም ስዕል ማድረግ ቻለ ማለት አይደለ? ይኼ ነው የትርጉም ልባስ የሚባለው። ይኼ ነው ለቅኔያዊው ፋይዳ አዲስ እሴት (Value) መጨመር የሚባለው።

በበኩሌ ሥነ ግጥም ከሌሎች የኪነ ጥበብ ዘውጉች ጋር ተዘምዶ ሲቀርብ አዲስ እሴት ለመጨመር እና ቅኔያዊ ፋይዳውን ለማጎልበት መሆን አለበት ባይ ነኝ። ለምሳሌ ከኋላ የሚያጅበው ሙዚቃ ሲኖር የሚያጅበው ሙዚቃ ግጥሙን የምናጣጥምበትን ሁናቴ (The Artistic Experience) የሚጨምር መሆን አለበት። ለዚህ ደግሞ የግጥሙን ስሜት ከግምት ያስገቡ ሙዚቃዎች ለዚህ ዓላማ ብቻ ተብለው መዘጋጀት አለባቸው። በዚህ በዚህ ከሎሬት ጸጋዬ ገብረ መድህን ጀምሮ እስከ አበባው መላኩ ድረስ ያሉ የግጥም ሲዲዎች የተሻለ ጥንቃቄ ነበራቸው። በተለይ አበባው መላኩ ይህንን ሃሳብ በደንብ የተረዳው ይመስለኛል። ግጥምን በጃዝ ስንልም ግጥምንም ሆነ ጃዝን ራሳቸውን እንደቻሉ የኪነጥበብ ዘውጎች ወስደን በሌላኛቸው መኖር ምክንያት ሁለቱንም ዘውጎች የምናጣጥምበትን ሁናቴ ትርጉም ባለው መልኩ እንዲያልቁት ብናደርግ መልካም ነው። ግጥሙ የጃዙን ውበት፣ ጃዙም የግጥሙን ውበት ማጉላት አለባቸው። እንዲህ ለማድረግ ደግሞ ሙዚቀኞቹ ከገጣሚዎቹ ጋር በግጥሙ ውስጥ ስለሚነሱ ሃሳቦች፣ ስለውክልናቸው ወዘተ በደንብ መወያየት ደጋግመውም መለማመድ አለባቸው።
እየሆነ ያለው ግን ይኼ አይመስለኝም። ሙዚቃዎቹም እንደው ከጀርባ ባዶ ከሚሆን ተብለው የሚገቡ ነው የሚመስሉት። ገጣሚያኑና ሙዚቀኞቹ በምትና በዜማ ጉዳይ አይናበቡም። ሁሉም የራሱን ስራ ብቻ ይሰራል። ይኼ ይኼ መስተካከል አለበት።

በሌላ መንገድ ደግሞ ጃዝ በግጥም ሊኖር ይችል ይሆናል፣ ሙዚቃው ተደርሶ ለእርሱ ግጥም መጻፍ። ጃዝ ካሉት ብቃቶች መካከል አንዱ ለድንገቴ ፈጠራ (Improvisation) የተመቸ መሆኑ ነው። ምናልባት በቅርቡ ግጥምም ከጃዝ ጋር በድንገቴ ፈጠራ ቀርቦ ወደመጀመርያው የሥነ ግጥም ዐውድ፣ ወደ ሥነ ቃል ከዋኔ ይመልሰን ይሆናል።

ሁለተኛው ልንጠነቀቅለት የሚገባው ነገር የጥገኝነቱ ጉዳይ ነው። ምን እየተለመደ መጣ መሰላችሁ? የግጥሙን ድክመት በጃዙ ፋንቻር አድበስብሶ ማለፍ፣ አልያም የሙዚቃውን ድክመት በግጥሙ መሸፋፈን። አንዳንዶቹ ግጥሞች ሙዚቃው ባይኖር እንክትክት ብለው የሚወድቁ፣ በራሳቸው መቆም የማይችሉ ናቸው። ይኼ ደግሞ 'ግጥም ያለማጀቢያ ሙዚቃ እንዴት ይቀርባል?' እስከ ማለት የሚደርስ ትውልድ እንዲፈጠር አደረገ። ይኼ ለሁለቱም ዘውጎች የማይጠቅም ነው ብዬ አስባለሁ።

ይኼን የምለው ስለጦቢያ መድረክ ብቻ አይደለም። ያልኳችሁ ነገሮች የጦብያ መድረክ ላይ እዚህ በጠቀስነው ሁናቴ ላይደረጉ ይችላሉ። ነገር ግን የጦቢያ ተጽዕኖ በየሶሻል ሚድያው እና በየአማተር የሥነ ጽሑፍ ክበባት ውስጥ በጣም ገናና እንደሆነ አይተናል። ይህ ተጽዕኖ ከአነባብ ጀምሮ እስከ ከዋኔ፣ አንዳንድ ሀረጎችንም (እንደ 'እና እንደነገርኩሽ...' ያሉ፣ እንደ 'እላለሁ!' ያሉ ጎዶሎ ተንጠልጣይ ስንኞችን ሳይቀር) እስከ መዋስ እና የአሪፍ ግጥሞች ምልክት እስከማስመሰል ድረስ ሄዷል። የጦቢያ ዓላማ አዲስ የከዋኔ ፈር ማሳየት ነው ብንልም እና ደግሞ ይኼ አዲስ ፈር ከላይ ያነሳናቸውን ራስን የመቻልና እሴት የመጨመር ጉዳይ እስካላጠፋ ድረስ የሚበረታታ ቢሆንም ትውልዱ ይህንን ዐውድ እንደብቸኛ ሕጋዊ የግጥም አቀራረብ ስልት የሚመለከተው ከሆነ ችግር ውስጥ ነን። ይህ የከዉኔ ዐውድ ሌሎቹን ዐውዶች የሚጫናቸውና የሚያጠፋቸው መሆን የለበትም። ለዚያ እኮ ነው ትውልዱ ውስጥ 'ግጥም እወዳለሁ!' የሚለው እንዲህ እንደአሸን ፈልቶ ሳለ መጽሐፍ ገዝተው የሚየነቡት ሰዎች ግን ጥቂት ሆነው የተገኙት። ለዚያ ነው ገብረ ክርስቶስ ደስታንና ከበደች ተክለአብን የማያውቁ ግጥም ወዳዶች ያፈራነው። ምን ያሳየናል ይኼ? እውነትም ፍቅራቸው ከግጥሙ ሳይሆን መድረኩ ከፈጠረው ድባብ... ምናልባትም ደግሞ ከጃዝ እና ከሙዚቃ ጋር መሆኑን ነው። ስለዚህ ሌሎች አማራጭ መድረኮች መብዛት አለባቸው። ግጥም በጃዝ ስህተቶቹን እርሞ ተጠናክሮ ይቀጥል። ግን ደግሞ ግጥም ብቻዋን ያለአጃቢ ያለጋሻ ጃግሬ ከትወና፣ ከሙዚቃ፣ ከዲስኩር፣ ከዝርው የሥነጽሑፍ ዘውጎችም ጭምር ተለይታ የምትቀርብበት፣ ግጥም ወዳድ ብቻ የሚገኝበት (በጦቢያ ዓይነት መድረኮች ግጥም የሚወድ ብቻ ላይገኝባቸው ይችላል።) መድረክ መኖር አለበት።

ማጉረምረም ሁለት - ቃከራና ሽለላ

ይቀጥላል...

ሽርሽር



አንበሳ የማይመስለው አንበሳ

በሚያዚያ 27 1933ዓ.ም አርበኞች ወራሪውን የፋሽስት ጦር ከሀገር ካባረሩ በኋላ ያደገው ከውጭ ሀገራት ጋር ያለ ግንኙነት ተከትሎ የሙዚቃው፣ የሥነሥዕል፣ የቴአትር፣ የሲኒማ ጥበብ መላመድ ፣ እንዲሁም በቴአትር ጥበብ ላይ ፍላጎት ያለው የተመልካች ቁጥር መጨመር አዲስ ቴአትር ቤት እንዲሰራ በ1943ዓ.ም የግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ፈቃድ ሆነ።

መጀመርያ ቴአትር ቤቱ ሊገነባ ፈቃድ የተሰጠው አሁን የአዲስ አበባ መስተዳድር ያለበት ቦታ ላይ የነበረ ሲሆን ኋላ ለጃንሆይ ሃያ አምስተኛ ዓመት የንግስ በዓል ማክበሪያ እንዲደርስ ስለተፈለገ "ቺኒማ ማርኮኒ" የተባለ ጣልያናው በግማሽ ጀምሮት የነበረው ሲኒማ ቤት ጋር (ማለትም አሁን የብሔራዊ ቴአትር ቤት የሚገኝበት ቦታ ጋር) ፣ ማዘጋጃ ቤቱ አጣርቶ ጣና ማጎበር የህንጻውን ግንባታ፣ጀ ሳልሞንጋ ደግሞ አደባባዩን እንዲሰሩ ተወሰነ።

በቴአትር ቤቱ አደባባይ ለቆመው ሀውልት እና በአዳራሹ መግቢያ ላይ ለቆሙት ሰባት ሀውልቶች ሥራ ጨረታ ተዘጋጅቶ <<ሞሪስ ካላስ>> አሸንፎ ከሙያ አጋሮቹ ጋር በመሆን በዋናው መግቢያ የሚታዩትን ስድስት ሀውልቶች ማለትም :- 4ቱ እህትማማቾች ጠበባት ፣ ትራጂዲን ፣ ኮሜዲን ፣ ዳንስ እና ሙዚቃን የሚመስሉ ቅርጾችን እንዲሁም በግራ እና በቀኝ የቆሙ ሁለት የእንስሳት ቅርጾችን እና የዘውዳዊው አገዛዝ ምልክት የሆነውን የይሁዳ አንበሳን ሥራ ጀመሩ።

የግርማዊነታቸውን የንግሥና የብር ኢዮቤልዩ ክብር አስመልክቶ የተቀረጸው ይህ ሀውልት (የይሁዳ አንበሳ) አስር ሜትር ቁመት ያለው ሲሆን ከጥቁር ድንጋይ እና ከጡብ የተቀረጸ ነው። ሀውልቱ ከሞደርን የሥነጠበብ ዘርፍ ይመደባል።

ይህ ሀውልት ከቴአትር ቤቱ 4ቀን ቀደም ብሎ ጥቅምት 30 ቀን 1948 ዓ.ም ከምሽቱ 11:00 የተመረቀ ሲሆን። በዕለቱም ንጉሠ ነገሥቱ ሀውልቱን ቀና ብለው ከተመለከቱት በኋላ "ነገሩስ አንበሳ አይመስልም ፣ የወጣበት ወጪ ግን አንበሳ ያስመስለዋል።" ብለው ተናግረዋል ይባላል።

በተናጠል ሀውልቱ ስንት እንደፈጀ ባይታወቅም የሙሉ የቴአትር ቤቱ የግንባታ ወጪ ግን 3.5 ሚሊዮን ብር እንደሆነ ሙያችን የተሰኘው በ2008 ዓ.ም በቴአትር ቤቱ የታተመው መጽሔት ያስረዳል።

ሀውልቱ በከተማው ጎልተው ከሚታዩ (LANDMARKS) ቅርሶች መሀል ሲሆን እንደ ከተማዋ ምልክትም ለመጠቀም ያስችላል። እንዲሁም የቀድሞ የኢትዮጵያ ቱሪዝም አርማ ነበር።



ወግ

አታምኑም አነዴ?

ደራሲ | መስዑድ ጀማል

እንደ አይጥ እየተሹለኮለኩ ነው ወደ ጎሬዬ የገባሁት። ከአከራዬ እይታ ለመሰወር ነው ይሄ ሁሉ። የአኗኗር ዘይቤዬ ከሰው ወደ አይጥ ከተቀየረ ትንሽ ቆየ። ቂጤን ብዳብስ አነስ ያለች ጅራት ሳላገኝ እቀራለሁ? እንደዚያም ሆኖ አምልጬ አላመልጥም። አዕምሮዬ እንደፀናፅል ይንኮሻኮሻል። መዓት ችግሮች ተሰግስገውበታል። የ 3 ወር የቤት ኪራይ አልከፈልኩም። ሥራ ቦታዬ ላይ የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶኛል። ፍቅረኛዬም በማላውቀው ምክንያት ከዘጋችኝ ሁለት ሳምንት አልፏታል። ኑሮ ስለከበደኝ ከፍለ ሃገር ላሉ ቤተሰቦቼ ብር መላክ አልቻልኩም፤ በዚህ ምክንያት አኩርፈውኛል። ችግሮች ሥርዓት ባለው ሰልፍ ተደርድረው ይከተሉኛል። ችግር የሚሰብ ማግኔት ውስጤ ማን እንደቀበረ አላውቅም።

ቤተሰቦቼ ‹አስቻለው› ብለው ስም ያወጡልኝ ይሄ ታይቷቸው ይሆን? ችግሮቼን ሳላውቅ እታቀፋቸዋለሁ መሰል በየሰዓቱ እየተፈለፈሉ ነው የሚሄዱት። ቤተሰቦቼ ግን "አስችለው" ነው "አስቻለው" ሊሉኝ የፈለጉት? በጊዜ ሂደት እየተቀየረ መጣ እንጂ መጀመሪያ ሀ ብለው ስሜን ሲያወጡልኝ "አስችለው" ያሉኝ ይመስለኛል።

ራቴን አልበላሁም። በዚህ ምሽት ልስራ ብልም የሆነ ነገር ይጎለኛል። እንጀራ ቢኖር ሽሮ ወይም በርበሬ አይኖረኝም። ሽሮውም እንጀራውም ካለኝ ብረት ድስቴ አልታጠበም ማለት ነው። ሁሉም ነገር ቢሟላ በርግጠኝነት መብራት ይሄዳል። ከሰል ላቀጣጥል ብል ደግሞ ሌላ ትልቅ ችግር አለ። ክብሪቶችን ላዛቸው አልችልም። ከመቼ እንደጀመረ ባይገባኝም አምፀውብኛል። ሲመስለኝ ይጠሉኛል፤ ገና ከመለኮሴ ፊታቸውን ያጠቁሩብኛል። እንዳንዶቹ ክብሪቶች ከብስጭታቸው ብዛት ጥርሳቸውን እሹለው ሊቀረጥፉኝ ወደጣቴ ይበራሉ። ቆይ ምን አደረግኳቸው? የቤት ዕቃዎቼም ተመካክረውብኝ ይሆናል'ኮ በየተራ የሚሰለቡብኝ። አሁን ያወራሁት ሃሜት ይሆንብኝ ይኾን? በቁስ ላይ ሃሜት ካለ እሱ ይወቅ።

ረሃቤ እየቆነጠጠው ሆዴ የሲታ ድምፅ ማውጣት ጀምሯል። ትዝ ሲለኝ ተገዝቶ የተቀመጠ ግማሹ ተበልቶ ግማሹ የቀረ ቆሎ አለ። ግን ለባዶ ሆዴ ደረቅ ቆሎ መላክ ባዶ ሮቶ በጠጠር እንደመደብደብ ነው። ተጨማሪ ጩኸት ከመፍጠር ውጭ ሌላ ምን ሊያመጣ? ከዚህ ሁሉ ጥቅል ብየ ብተኛስ?! ግን እንደተለቀቀ ቤት እና የሆነው ሆዴ ያስተኛኛል? አይመስለኝም። አፍ ቢኖረው " እሪ" ነበር የሚለው።

እንቅልፍ እንዲወስደኝ የሆዴን አለቃ ማታለል እንዳለብኝ ተሰማኝ፤ አዕምሮዬን። ተነስቼ ቦርጫሟን ቴሌቪዢኔን ከፈትኩ። መዝናኛ ፕሮግራም ላይ አድርጌ አዕምሮዬ ረሀቡን እንዲረሳ ላደርግ ነው ሃሳቤ። ህህህ... ይሄን ጂኒየስነቴን አለቃዬ ቢያውቅ እድገት እንጅ ማስጠንቀቂያ አይሰጠኝም ነበር። ይሄ እንከፍ ...የስራ ልምድ እንጅ እውቀት መች አለው?

ቲቪዬ ወከክ አለች። መጀመሪያ ብርሃን ነው እንጅ ምስል አትከስትም። ከምስሉ በፊት ደግሞ ሁልጊዜ ድምጿ ይፈጥናል። የቲቪዬን እነሳስ በዓይነሕሊናዬ በሰውኛ እነሳስ ተክቼ ስመስለው... ከእንቅልፏ በመቀስቀሷ እየተበሰጫጨች ከወዲያ ወዲህ ተገለባብጣ፤ ተለጥጣ፤ በስተመጨረሻም እየተንጠራራች ተነስታ

ዓይኗን በእይበሉባዋ እየሞዠቀች፡ ዓይናሯን አራግፋ ዓይኗን እስከምትገልጥ... ማፏሸኳ ቀድሞ የሚሰማ-እንደዚያ ይመስለኛል።

ቲቪዩ ምስል ስትከስት እና እንድ የመዝናኛ ፕሮግራም ሲጀምር ተገላጠመ። ጋዜጠኛዋ ፕሮግራሙን እያስተዋወቀች ነው...

" ውድ ተመልካቾቻችን ‹አታምኑም እንዴ?› የተሰኘው ሳምንታዊ የመዝናኛ ፕሮግራማችን ተጀምሯል። ዛሬም በአንድ ልዩ ፕሮግራም መጥተናል። ‘በሀገራችን ያለው ስም አወጣጥ ከአወላለዳችን ጋር ያለው ትስስር ምን ይመስላል?’ የሚለውን ልናስቃኛችሁ ወደን፡ በርከት ያሉ እንግዶችን ጋብዘናል።"

በቴሌቪዥኔ መስኮት ውስጥ የተለያዩ ሰዎች ይታያሉ። ሴት፡ ወንድ፡ ወጣት፡ ሽማግሌ ስቱዲዮውን ሞልተውታል። በአጭሩ በቦርጫሟ ትሪዬ የሰው በያይነት ቀርቧል ማለት ይቻላል።

በጉርምስና ዕድሜው ጠረንጴዛ የነበረው የቲቪ ማስቀመጫዬ ካለወትሮው “ሲጢጢጥ” ማለት ጀምሯል። ሰዎቹ ናቸው ወይስ ቲቪዬ ናት የከበደችው? “ሲጢጥ” የሚለውን የጣውላ ዘርን ቃል ወደ አዳም ዘር ቃል ስንመነዝረው "እህህ" የሚል ማቃሰትን ይሰጠናል።

በድንገት የክፍሌ በራፍ ተቆረቆረ። ሳላውቅ የሆነ ችግሬን ታቀፍኩት መሰለኝ ይሄው ሴላ ችግር ተፈለፈለ። እከራዬ ናቸው። በበራፌ መስኮት ላይ በተሳለው ጥላ ነው ያወቅኳቸው። ባርኔጣ ማድረግ ይወዳሉ። ርሳቸው ለብርዱ ነው ቢሉም እኔ ግን ሁልግዜ ባርኔጣ ማድረግ ለምን እንደሚወዱ አውቃለሁ። ሞላላ እናታቸውን ለመሸፈን ነው። እናታቸው በእንድ በኩል ያጋደለ ነው። እንድ ቀን ፀጉራቸውን ሲታጠቡ ነው ያየኋቸው። እርቃናቸውን የሆኑ ያህል ነው ስለሚሰማቸው ባርኔጣቸውን ከእናታቸው ሲደፉ ፀጉራቸው እሰኪደርቅ ራሱ መታገስ አይችሉም።

ትዕግስታቸው ራሱ ትዕግስት እንዳጣ ይሰማኛል። በቃ "ነገ ጓዝህን ይዘህ ውልቅ በልልኝ" ሊሉኝ ነው። ይህንን ቤት ማጣት አልፈልግም። እንደኛ ለሥራ ቦታዬ በጣም ቅርብ ነው። መብራትና ውሀ ሳልሳቀቅ እንድጠቀም ፈቅደውልኛል። ያው የመብራት ሀይልንና የውሃልማት መልካም ፈቃድ ቢቀድምም። የተከራየሁትም በጥሩ ዋጋ ነው። ቤቱም ጥሩ ነው ለኔ... ያው እንደማንኛውም ቤት የሆነ የአይጥ ጎሳ በኮርኒሴ አዳብዬ ብናርም፡ ነገር ግን እንድም ቀን የቤት ኪራይም ሆነ የአስቤዛ ጠይቄያቸው አላውቅም። እኔው ተንኩሻቸው ነው እንጂ አከራዮቼም ጥሩ ሰዎች ናቸው። በተለይ የቤት ኪራይ ስከፍል።

በራፉ በድጋሚ ተንኳኳኳ። እንደሚፈለፈሉት ችግሮቼ ምናለ አከራዬን የማሳምንበት አንድ ምክንያት መፈልፈል ብችል?

ተነስቼ በሩን በትህትና ከፈትሁ። አከራዬ ጋሽ ዱባለ ልክ እንደነዛ ክርቢቶች ፊታቸውን ከስክሰው ቆመዋል። ምን ሊሉኝ ይሆን? በሩን የያዝኩበት እንጂ በስሱ ሲንቀጠቀጥ ይሰማኛል።

በፀጥታ በሩን ገፋ አድርገው ወደውስጥ እየዘለቁ "ግባ" ብለው ጋበዙኝ። በገዛ ቤቴ እየጋበዙኝ ነው? ... በቃ አባረሩኝ ማለት ነው? ኡፍፍ፡ እረ አይደለም! የጋሽ ዱባለ ሰፊ ትከሻ የሸፈናቸው ጓደኞቸው ጋሽ አናጋው ለካ ከኋላ ነበሩ። በእንዴ ፍርሀቴ ብን ብሎ ጠፋ። ጋሽ አናጋው ቀለል ያሉ ሰው ናቸው። እሳቸው ባይኖሩ ኖሮ ከዚህ ቤት ጥንት ነበር የምባረረው። እከራዬ ሲቆጡ እያሳሳቁና እያለሳለሱ እዚህ ቤት እንድከርም ያደረጉት እሳቸው ናቸው። በጣም ተጫዋች እና ተግባቢ። እናታቸው ገና ስትወልዳቸው መሞቷን እና በስንት ልፋት አሁን ያሉበት ደረጃ መድረሳቸውን ሲያወሩ ሰምቻለሁ። በአጭሩ ወደቤቱ እሳትና ውሀ ናቸው የገቡት። እሳቱ ቢነሳም ማጥፊያው ስላለ ተረጋጋሁ።

ቶሎ ብዬ ወንበር አስያዝኳቸው። ቶሎ ብየ፡ቅድም ለባዶ ሆዴ የነፈግኩትን ቆሎ በሳህን አድርጌ አስዘገንኳቸው። ቆሏቸውን እየቆረጠሙ በፀጥታ ተቀምጠው ወደ ቲቪዬ አፈጠጡ። ዋናው ነገር ዓይኖቻቸው ከእኔ መሸሹ ነው። ቶሎ ብዬ የቲቪየን ድምፅ እየጨመርኩ፡ "በጣም ቆንጆ ፕሮግራም ነው፡ እሱን እያየሁ እያለ ነው የመጣችሁት፡ የሚያዝናና ፕሮግራም። አትከታተሉትም እንዴ?" አልኳቸው። የምለው ሳጣ ነው እንጂ እኔ ራሱ ዛሬ ነው ያየሁት።

ጋዜጠኛዋ ትቅለበለባለች።

“ከማስታወቂያ በኋላ ተመልሰናል። ቀደም ብዬ እንዳስተዋወቅኳችሁ፡ ‘የወጣልን ስም ከአወላለዳችን

ጋር ዝምድና ነበረው፣ ያሉ ሰዎችን እዚህ ስቱዲዮ ጋብዘናቸዋል።" ፊቷን ወደ አንድ ወጣት ልጅ አዞረች። ከቅድም ጀምሮ ብቻውን ሲገለፍጥ እያየሁት ነበር። "ካንተ ልጀምር። ራስህን ለተመልካቾች አስተዋውቅና ስምህ በምን ምክንያት ሊወጣልህ እንደቻለ አጫውተን?"

የተጠየቀው ሰው ድንገት ከት ብሎ ሳቀ። ጋዜጠኛዋ ግራ በመጋባት አየችው። ሰውየው ግን በሳቁ ላይ ሌላ ሳቅ እየደረበ ይንፈቀፈቅ ጀመር። እንደምንም ሳቁን ለመግታት እየታገለ፣ "ይቅርታ፣ ሃሃሃ... ስሜ... ቂቂቂቂ... ስሜ ይስሐቅ ይባላል... ቂቂቂ... ልክ ከእናቴ ማህፀን እንደወጣሁ ነው... ሃሃሃ... ስሜ የወጣልኝ..."

"እሺ አቶ ይስሐቅ፣ ስምህ በምን ምክንያትና አጋጣሚ ሊወጣልህ እንደቻለ ለኔም ለተመልካቾች ብትነግረን?"

"እሺ... ሃሃሃ... 'ይስሐቅ' ብሎ ስሜን ያወጣልኝ አባቴ ነው። ቂቂቂ... እኔ ስወለድ እንደሌሎቹ ህፃናት.... እያለቀስኩ... እየጮኽኩ ምናምን አልነበረም። ቂቂቂ... በሳቅ በፈገግታ ታጅቤ... እየተንከተከትኩ ነበር ከእናቴ ማህፀን የወጣሁት። ሂሂሂ... ጭንቀትና ስቃይ ውስጥ የነበረችው እናቴ... ቂቂቂ... ሳቁን ስታይ 'ምን ጉድ ነው?' ብላ ተገርማ አብራኝ መሳቅ ጀመረች። የነገሩኝን ነው የማወራሽ። ሆስፒታል ውስጥ የነበሩ ሁሉም አፋቸውን ከፍተው ቀሩ። ከዛም በኋላ ደግሞ ሌላ የሚያስደንቅ ነገር ተከሰተ... ቂቂቂ..."

"ምን?" ጋዜጠኛዋ ለመስማት ጓጉታ ጠየቀች፣

"በዚያች ደም ባወዛት ሚጢጢ መዳፌ... ቂቂቂ... ጭምድድ አድርጌ የያዝኩት ነገር እንዳለ እናቴ ተመለከተች። ሃሃሃ... ምን እንደሆነ ለማየት ጣቶቼን ለማላቀቅ ብትሞክርም ወይ ፍንክች! ቂቂቂ... 'ምን ጉድ ነው?' ብለው ከአዋላጇ ጋር ተባብረው በግድ እጄን አላቅቀው ቢያዩ ምን ቢያገኙ ጥሩ ነው?... መፋቂያ... ቂቂቂቂ... 'ታምኛለሽ፣ አታምኚም?'"

"በጣም ይገርማል" አለች በማዳነቅ።

" ሃሃሃ... ከዚያ በኋላ ሁሉም በሳቁ ስቀውና ተገርመው ከጨረሱ በኋላ... ቂቂቂ... ወደ አባቴ እቅፍ አስገቡኝ። አባቴም...ሂሂሂ...ከጭንቀት ወደ ሳቅ ያሸጋገርኩትን እኔን እያየ...'እንዳተስ ያለ ልጅ ሁልግዜ ይወለድ...ዘላለም ይሳቅ...' ብሎ ስሜን ይስሐቅ አለው። ቂቂቂ..."

"በጣም ይገርማል አቶ ይስሐቅ...እንደነገርከኝ ከሆነ እየሳቅክ ነው የተወለድከው... ይሄ ሳቅህ ከምን የመነጨ ነው? ወደ ሀኪሞች ዘንድስ ሄደህ ለመታከም አልሞከርክም?"

"ቂቂቂ...እውነት ለመናገር ለመታከም ሞክሬ አላውቅም ነበር... ሳቅ ተገኝቶ ነው? ...ሃሃሃ"

እንዴት እንዴት ነው የሚገለፍጠው?....ጥርሱን ምች አይመታውም?....ቆይ ምን አግኝቶ ነው?

" ሳቅ...ህህህ....ስንት ሰው ያጣው ነገርኮ ነው። አሁን ግን ግዜው ጨፍግጓል። ሳልፈልግ በግድ ሃሳቤን ለመቀየር ተገደድኩ። ሃሃሃ...ሰው ሆድ ብሶታል 'በማናባህ ነው የምትስቀው?' የሚለኝ ሰው ቀስ በቀስ እየበዛ መጣ። ስስቅ 'ምን ሞልቶልህ ነው እንዴህ የምትንከተከተው?' መባል ጀመርኩ። እንዳውም ይሄን ሳቁን ከፖለቲካ ጋር አያያዙት። 'የእከሌ ፓርቲ አባል ስለሆነ ነው' እባል ጀመር። ከዚህ በኋላ ነበር ይሄ ሳቁ በዚህ ዘመን እንደማያኖረኝ የተረዳሁት። ሃሃሃ...የሳቁ መድረክ የእይታ ግዜውን ስለጨረሰ የከንፈሮቹን መጋረጃ መግጠም አለብኝ ብዬ አሰብኩ። ቂቂቂ...የዛሬ ሰው ብሶቱን ተጋርቶ የሚያላቅሰው ነው የሚፈልገው። ህህህ... እናም ለመታከም ወስኜ ብዙ ቦታ ዞርኩኝ። ሃሃሃ... ነገር ግን የትኛውም ዶክተር፣ እንኳን ሊያክመኝ የህመሜን ስም እንኳ አላወቁትም ነበር። ሃሃሃ.... በኋላ ላይ ተስፋ ቆርጬ በተቀመጥኩበት ሰዓት፣ በቴሌግራም 'መሪጌታ አታለል' ከሚባሉ ሰው ጋ ተዋወቅኩኝና 'የብብት ስንፈት' እንዳለብኝ ነገሩኝ። የሆነ የሚቀባ ነገር ሰጥተውኝ ህክምናዬን እየተከታተልኩ ነው። ቂቂቂ....እየሽ ጊዜን መምሰል አለብሽ፣ ምክንያቱም ጊዜ እንችን እይመስልማ...ሃሃሃ"

"ውድ ተመልካቾቻችን ተወዳጁ "አታምኑም እንዴ?" ፕሮግራማችን እንደቀጠለ ነው። አሁንም አብሮነታችሁን ከእኛ ጋር እንድታደርጉ የአክብሮት ግብዣችን ነው...ወደ ቀጣዩ እንግዳችን አልፈናል።"

በቴሌቪዥኑ ጠይም ጎልማሳ ሰው ብቅ አለ። "ስሜ 'ማህሙድ' ይባላል። ስሜን 'ማህሙድ' ያሉት ብዙ ሰዎች ቢሆኑም ያፀደቀው ግን አባቴ ነው።"ብሎ ጀመረ፣

ጋዜጠኛዋ ለወሬው ሰፍ ማለቷ ከሁኔታዋ ያስታውቃል።

"እስኪ ከመጀመሪያው ጀምሮ ሁሉንም አጫውተኝ?"



“ይሄውልሽ እኔ ስወለድ እንደማንኛውም ህፃን እየተነፋረቅኩ አልነበረም። ወይም ደግሞ እንደ አቶ ይስሃቅ በሳቅ እየተንከተከትኩ አልነበረም የተወለድኩት:: የኔ አወላለድ ከመላው ዓለም ህፃናት ለየት ያለ ነበር።”

“እንዴት?” አለች ጋዜጠኛዋ።

“እንዴት ማለት ጥሩ። ከእናቴ ማህጸን ልክ ስወጣ፣ አዋላጇ በአኳኋኔ ግራ ተጋባች። ‘አውራ ጣት የምታህለውን የእግሬን መዳፍ ከፍ ዝቅ አደርግ ነበር’ አሉ። ልክ በእግሬ መሬት እንደምተመትም። ልክ በሆነ ዜማ ውስጡ እንደተነካ ሰው። መች በዚህ ብቻ አቆምኩ... ከእናቴ ማህጸን ወጥቼ በአዋላጇ እጅ በጨርቅ ሽብ ስደረግ ደሞ ሙቀት ተሰማኝ መሰል ባሰብኝ። እኒያን ሚጢጢየ ከንፈሮቼን አሹዬ ማኘጨት ጀመርኩ። ይሄ ሁሉ ሲሆን ዓይኔ እንኳ አልተገለጠም ነበር። ታዲያ የነገሩኝን ነው የማወጋሽ...”

ጋዜጠኛዋ በመገረም አኟን ከፍታ እያዳመጠችው ነው። ልክ አዲስ ተረት እየሰማ እንዳለ ህፃን ልጅ። እሱም ይሄን መገረሚን አይቶ፣

“አትገረሚ! የሚያስገርመው ነገር ገና ነው። ቀጠልኩልሽና ለምልክት ከእጇ ላይ የተሰኩ የሚመስሉትን ፅንሰ አውራ ጣቴን ከመሃል ጣቴ እያፋጨሁ ድምፅ ማውጣት ጀመርኩ። የሆነ ሪትም ተፈጠረ። ከነዚያ ትናንሽ ጣቶቼ ድምጽ መውጣቱ ሲገርማቸው፣ ይባሱኑ ከጉሮሮዬ ጎርነን ያለ ድምጽ ይወጣ ጀመር። ታምኛለሽ፣ አታምኝም?! ወጣ! እግሬን እየተመተምኩ፣ጣቶቼን እያፏጨሁ... መዝፈን ጀመርኩ። የማህሙድን ዘፈን። ’ገና መናገር ሳትችል እንዴት ዘለህ መዝፈን ቻልክ? ዜማና ግጥም አቀናጅቶ እንዴት አንድ ጨቅላ ይዘፍናል’ እያልሽ ነው አይደል በውስጥሽ?!...ግን በቃ መዝፈን ጀመርኩ። የማህሙድን ‘የሺ ሃረጊቱን’ ማንቆርቆር ጀመርኩ፣

የሺ ሀረጊቱ የክቲቱ
የኔ ዘረ ብዙ
ስንቱን ደጅ ልጥና ልማለድ
ይጠሽ እስክነጉድ....

...እያልኩ የማህሙድን ሙዚቃ ማዜም ጀመርኩ። ሆስፒታሉ ጸጥ ረጭ አለ። ሲነፋረቁ የነበሩ ጨቅላ ህፃናት ሳይቀሩ ፀጥ አሉ። እናቴ አኟን ይዛ ቀረች።”

ቆይ ምን እየተፈጠረ ነው? ይሄን የሚያስማኝ ጣቢያው ነው? ወይስ ይች ኑሮ በቃኝ ያለች ቴሌቪዥኔ? ወይስ ከመጠን በላይ የተወጠረው አዕምሮዬ? ...እንጃ የሆነ ነገር ግን አልተብራራልኝም።

“ ከዛልሽ ቀጠልኩና...

‘እንደምን ይወድቃል እንደዘበት
ያደረግነው ሁሉ በልጅነት
ፍቅር እንደፈሳሽ ይሆናል ወይ
ለምን ዘነጋሽ ተረሳሽ ወይ
...ተረሳሽ ሆይ....አሃ አሃ ተረሳሽ ወይ?’

እያልኩ መዝፈን ጀመርኩ። ይህን ግዜ የሚቀበለኝ ሰውም አግኝቼ ነበር። ሆስፒታሉን ለአጭር ሰዓት ኮንሰርት አደረግኩት። ‘አዋላጆቼ እና ሌሎች ድርስ ሴቶች መጀመሪያ ላይ ግራ ቢጋቡም ትንሽ ቆይተው ግን በእኔ ዘፈን እየተዝናኑ እና እየተወዛወዙ ነበር’ አሉ። ይሄ ሁሉ ሲሆን በአዋላጇ እቅፍ ስር ነበርኩ....ድንጋጤ ሰራዋን እንዳትሰራ አድርጓት ነበር::

ነበርኩ....ድንጋጤ ስራዋን እንዳትሰራ አድርጓት ነበር።

ትንሽ አረፍ አልኩና ደግሞ ...መቀስ ያልነካውን እትብቴን በግራ እጇ ወጠር አድርጌ ያዝኩና ልክ እንደከራር በቀኝ እጇ እየገረፍኩ በትዝታ...

ስንቱን አስታወስኩት ስንቱን አሰብኩት
ልቤን በትዝታ ወዲያ እየላኩት
አንዴ በመከራ አሃ አንዴ በደስታዬ
ስንቱን ያሳየኛል አሃ ትዝታዬ...

እያልኩ በሚያስረቀርቅ ድምፄ እንጉራጎርኩ። በዚህ ጊዜ እናቴን ጨምሮ ሁሉንም አስለቀስኳቸው። አድናቆታቸውን በጭብጨባ ገለጹልኝ። ለካ አባቴም እንግዳ ድምፅ ሰምቶ ገብቶ ሁሉንም ነገር በአድናቆት ሲከታተል ኖሯል። የሚስቱን የጭንቀትና የስቃይ ጩኸት በዜማ የቀየርኩለትን ልጁን አቅፎ በትኩረት ካየኝ በኋላ 'ትንሹ ማህሙድ' ብሎ ሰየመኝ።"

"ግን በዚህ እድሜህ እንዴት ግጥምና ዜማን አሳክተህ ልትዘፍን ቻልክ? ለኔ አዲስ ነገር ይመስለኛል?" ጠየቀች ጋዜጠኛዋ።

"የተወለድኩ ሰዓት ጀብዴ ተሰምቶ ጋዜጠኞች መጥተው ወሬው ብዙ ሰዎች ዘንድ ደረሰ። ውቅያኖስን ተሻግሮ ፈረንጆች ዘንድም ደርሶ ስለነበር፤ አዲስ ነገር የማያመልጣቸው እነአጅሬ እያነፈነፉ መጥተው አጥንተውኝ ነበር አሉ።"

"እውነት?...ታዲያ ምን አሉ?"

"እነሱ እንደሚሉት ከሆነ... 'ከ7 ቢሊየን ህዝብ ውስጥ በአንዱ ላይ የሚከሰት ነው'፤ እናትና እና አባቴ ከተፀነስኩበት ሰዓት ጀምሮ የማህሙድን ዘፈን አብዝተው ያዳምጡ ስለነበር በዚያ ምክንያት ሊሆን እንደሚችል ነው መላምታቸውን ያስቀመጡት።"

"በጣም የሚደንቅ ነገር ነው የነገርከኝ አቶ ማህሙድ። ውድ ተመልካቾቻችን 'አታምኑም እንዴ?' የተሰኘው ተወዳጅ ፕሮግራማችን እንደቀጠለ ነው...."

ጋዜጠኛዋ ፊት ላይ ምንም እንግዳ ነገር አይነበብም። ሁኔታዋ የጤነኛ ሰው የሚባል ነው። እንዴት እንደሆነ አልገባኝም። ፊቷን ለአዲስ ግርምት እያመቻቸች ወደ ሶስተኛ እንግዳዋ ፊቷን አዞረች።

"እሽ አባቴ ስምዎትን ይንገሩንና እንዴት ሊወጣልዎት እንደቻለ አጫውቱኝ?"

ዕድሜ የጠገቡ ለአዛውንትነት የቀረቡ ሽማግሌ ናቸው። ነጭ ሪዛቸውን እየላጉ ነው የሚያወሩት። "ስሜ ደም መላሽ ይባላል፤ በርግጥ ይሄ ስም ቀላል አይደለም። እንዲውም ስም ሳይሆን ኃላፊነት ነው።"

ጋዜጠኛዋ የተደረደሩትን እንግዶቿን እስከታዳርስ የቸኮለች ትመስላለች። ሽማግሌው ወደ ገደለው እንዲገቡ በመፈለግ፤ "ታዲያ ደም መላሽ የሚለው ስምዎት ከአወላለዶት ጋር ምንድነው የሚያገናኘው?" ብላ ጠየቀች።

"ልመጣልሽ አይደል፤ እናቴ ከኔ በፊት አንድዜ ልትወልድ ብላ ከሞት ደጃፍ ነበር የተመለሰች፤ የዚያኔ ጨቅላውም ሞተባት፤ እናቴም ብዙ ደም ፈሷት ነበር። እንዳው ለጥቂት ነው ከመልዓከ ሞት ጋር የተላለፉት..."

ጋዜጠኛዋ ራሷን ከፍ ዝቅ ታደርጋለች። የራሷን ከፍና ዝቅ ማድረግ ሰምና ወርቅ አለው። ሰሙ እያዳመጥኮት ነው ሲሆን፤ ወርቁ ደሞ ቶሎ ቶሎ ተናገሩ የሚል ነው።

"ከጊዜያት በኋላ እኔ ተፀነስኩ። ሲያወጡኝ የእናቴ ሆድ አለቅጥ ተነርቶ ነበር። የቀዬው ሰው ሁላ ሰጋ...' አየ አሁንስ አትተርፍም፤ ገዳዩዋን ነው የተሸከመችው' ተባለች። የማይደርስ ቀን የለም ያ ቀን ደረሰ። የእናቴ ምጥ መጣ። የቀዬው ታዋቂ አዋላጅ ተጠራች። 'አልመጣም' ብላ በስንት መከራ ተለምና ነበር የመጣችው። 'ፈርታ ነው' አሉ። ጎጇችን በሴቶች ተሞላ። እናቴን ሊያጠነክሩ፤ አይዞሽ ሊሉ መሆኑ ነው....ክክክ" ብለው ሳቁ፤ ያሳቃቸው ምን እንደሆነ ጋዜጠኛዋ ሊገባት አልቻለም።

"አባቴ በጭንቀት ቀበቶውን ሲያላላ፤ 'ቦላሌውን ከወገቡ እንዳጣው' ነፍስ ሳውቅ ነግሮኛል... ክክክ ምን ዋጋ አለው? ያንን ሁሉ ትርኢት እኔ ደም መላሽ መና አስቀረሁት። የዚያን ምሽት እናቴ አላማጠችም... አልጮኸችም ነበር። ገና 'እ' ከማለቷ ብቅ አልኩ። ማንም አላመነም ነበር። ክክክ...ከእሷ ደሞ የእኔ ይባስ::ለቅሶ ይቅርና ትንፋሼም አይሰማም ነበር። ቆፍጠን ብዬ ነበር የተወለድኩት።

ታዲያ የነገሩኝን ነው የማወጋሽ።

አባቴ ተጠርቶ ገባ። ምሽቱን ሲያያት እንኳን የወለደች ያነሰራትም አትመስልም ነበር። ልቡ በደስታ ቦረቀች። ተጠቅልዬ ወደተቀመጥኩት ወደኔ መጥቶ አየኝ። ጡትም አላሰኘኝ፤እንዲሁ ዝም ብየ አውራ ጣቱን እመጠምጣለሁ። ቆፍጣና ነበርኩ ከያኔውም። 'እረ እንዴት ያለ ልጅ ተወለደ?' አለ አባቴ ተገርሞ... ለሰዓታት በትዝብት ከተመለከተኝ በኋላ ስሜን 'ደም መላሽ' ብሎ አወጣልኝ።"

ጋዜጠኛዋ ፊቷን ወደካሜራ እያዞረች "ተመልካቾቻችን አሁንም አብሮነታችሁን እስከመጨረሻው ከእኛ ጋር እንድታደርጉ የአከብሮት ግብዣችን ነው... እንግዶቻችን አላለቁም... ከመልዕክት በኋላ ከወ/ሮ አሰለፈችና ከጋሽ ተፈራ ጋር ቆይታችንን የምንቀጥል ይሆናል..."

ድንገት ከገባሁበት ሰመመን እንደመባተት አልኩ። "የእኔም ስም በዚህ መንገድ ወጥቶልኝ ይሆን?" ብዬ በሃሳብ ባህር ጠልቄ ነበር። ወይኔ ጉዴ!! ከቤቴ አስገብቼ ያስቀመጥኳቸውን ጋሽ ዱባለንና ጋሽ አናጋውን ዘንግቻቸው ነበር። ዞሬ ሳያቸው እነሱም እኔ ሰጥሜበት በነበረው የሃሳብ ባህር ተዘፍቀዋል ወይኔ አለቀልኝ! እነሱም ስማቸውን በዚህ ቀውስ ፕሮግራም መንገድ እየፈቱት እንዳይሆን!?

ፊታቸው ቀስበቀስ እሳት እንደተጠጋው ፕላስቲክ ሲኮማተር ይታወቀኛል። ፊታቸውን ያኮማተረው ቁጣ እንደሆነ ለማወቅ ሰከንድ አልፈጀብኝም። "አንተ ወኔውን ብታጣ በዚች ቴሌቪዥንህ አሰደብከን!" የሚሉ ይመስላሉ። እጃቸው ጋር የነበሩትን ቆሎዎች ወደሳህኑ አራገፉ። ምን ሊያደርጉ ነው? የተመካከሩ ይመስል ሁለቱም ከወንበራቸው እኩል ተስፈንጥረው ተነሱ። ከጋሽ ዱባለ፣ ጋሽ አናጋው የበለጠ ተናደዋል። ወደ ጋሽ ዱባለ ፊታቸውን እያዞሩ፤

"ይቅር በለኝ...እስከዛሬ ለካ እንዲህ ያለውን ባለጌ ነበር ነበር እሹሩሩ ስትል የነበረው?!"
"ነግሬህ ነበር'ኮ...አልሰማ አልከኝ እንጂ"
"በል ውሳኔህን ወስን...እስከዛሬ የርጎ ዝንብ ሁኜ ላስቸገርኩህ ይቅር በለኝ"

የትኛው ውሃ የትኛው እሳት እንደሆኑ ለመለየት አቃተኝ። አኳኋናቸው አፍ አውጥቶ የሚናገረው ነገር ቢኖርም ውስጤ ግን ለመቀበል አልፈለገም። ከአፋቸው ቃል ሁኖ እስኪወጣ እየጠበቅኩ ነው።
ጋሽ ዱባለ ከአፋቸው መስማት የማልፈልገውን ቃል አወጡ፤

"በል ከነገ ጀምሮ ጓዝህን ጠቅልለህ ከቤቴ ውልቅ በልልኝ!" ብለው ባልንጀራቸውን አስከትለው ከቤቴ ማለቴ ከቤታቸው ወጡ።

በቃ? አለቀ? እንዲህ እንደቀላል? ነገሮች በፍጥነት የሄዱበት መንገድ ደነቀኝ። የሰው ልጅ አይደለሁ? ምክንያት መፈለግ ጀመርኩ። በንዴት ደም የመሰለው ዓይኔ ወደ ቴሌቪዥኔ አነጣጥሯል። ቆይ ቲቪዬ ምን ታድርግ? ጉድ ያደረገኝ ይሄ ቀውስ ፕሮግራም ነው... አዎ! ይሄ 'እታምኑም እንዴ?' ስትለው የነበረው ፕሮግራም ነው።

"እዝናናበታለሁ" ብዬ የከፈትኩት ፕሮግራም "እሳቀቅበታለሁ" ብዬ እንድም ቀን አስቤ አላውቅም ነበር። "አረፍ እልባቸዋለሁ፤መንፈሴን አድስባቸዋለሁ" ያልኳቸው ፕሮግራሞች ህይወቴን ያመሰቃቅሉታል ብዬ መች አስቤ አውቅና? እንዴ አስችለው ተብያለሁ... እንግዲህ መቻል ነው!

አርኬ

ድሮ
ቃል እንደ እጅ እግሬ ~ ይታዘዘኝ
ቅኔ እንደ ወንዝ ፏፏቴ ~ ይፈስልኝ
ግጥም እንደ ጡብ ~ ይሰደርልኝ
የነበርኩ ባለቅኔ
ላንዲት ጉብል ቆንጂትዬ እጅ ሰጠሁ
በሌት በርኖስ በቀን መብረቅ ተሰነጠቅሁ።


ቅኔ ምን ሊጠቅም
ምን ሊበጀን ግጥም?

አለማወቄ ነው የኔ መንገድ
ቃል ጠፋኝ ቅኔ አጣሁ
አንድ የምችለው ባንቺ ፍቅር መንደድ።

ልቀኝልሽ ቃል አጣሁ
ልጽፍልሽ አቅም አነሰኝ
የአፍቃሪ ሰው ግብሩ (ለወደዳት እንስት)
ግጥም መጻፍ አይደል
አይደል ቅኔ መዝረፍ
ከጥርሷ ለሚፈልቅ ከሳቋ ፏፏቴ
ቢቻል ሦስት ሱባዔ ካልሆነም ሁለቱ
ይጠመቅ!

ቃላትን አይደለም
ግዜውም አይበቃም
ሀሳብ እሱነቱን ህይወቱን በሙሉ
ይሰዋ!

እንቆቅልሽ



1ኛ ደረጀ ፈንጭ

ወደጎን

1. በእስልምና፡ የበታ የነታ አዋቂ ሰው(3)
2. በዘፈን ግጥሞጀ እና በጋዜጠኝነቷ የምትታወቅ ገጣሚ(6)
3. የነገሮች መነሻ፡ ጥንት(5)
4.የመጀመርያው የኢትዮጵያ ባለ ቀለም ፊልም(2)
5. ወትሮም አልታወቀ መሐጃ መምጫሺ ...(7)
6. ምግብ፡ ከሠማይ የሚወርድ(2)
7. የረዳት ፕሮፌሰር ደበበ ሠይፉ ድርሰት የሆነ ቲያትር(9)
8. ጥግ(4)
9. ፀሐይ(4)
10. ጮርናቄ(3)
12. እኔ እና አንቺማ እንታረም ...(5)
13. pre-(3)
14. ፍርድ ቤት፡ ዳኝነት(3)
15. በጎንደር ዘመነ መንግስት የነበረ የታወቀ ባለቅኔ(7)
30. ...የጹርዬ ምሳ(4)

ወደታች

1.ቧልት፡ ጨዋታ(5)
16. ወንድዬ አሊ(5)
17. ተጎድቶ(4)
8. መስጠት(5)
18. የከበረ ድንጋይ(3)
19.የከፍተኛ ትምህርተ ዘይቤ(3)
20. ድር እና ማግ፡ መወርወርያ በእጁ ናቸው።(3)
21. የዮፍታሔ ንጉሤ ቲአትር(5)
22. ሙዳይ፡ ልክ እንደ ፓንዶራ(3)
23. ለሻዬ የሚያገለግል መእዘኛ ቅጠል፡ ወዲያውም የከረሜላ ስም(2)
24.Period በአማርኛ (As in Interval of Time)(5)
25. ኮምፕዩተር(5)
26. መቀመጫ፡ ወንበር ፡ ግን የበለጠ ክብር ያለው(4)
27.ሞቶ የማይቀበር ወድቆ የማይሰበር አባቴ የሰጡኝ ወንበር (2)
31. ታሬሳ(4)

አግድም

28. የኢትዮጵያ ጀግና በሮማ፡ ለገሐር፡ piazza dei cinquecento፡ ዶጋሊ(4)
29. ከንፍ የለኝም እበራለሁ፡ ዓይን የለኝም አለቅሳለሁ(3)

2ኛ ደረጃ ፍንጭ

ወደኅን

2. በነጭ ሽብር የተገደለች(5)
3. የመጽሐፍ ቅዱስ የመጀመርያ ክፍል(5)
4. ለሚች ወገን የሚከፈል የነፍስ ዋጋ፡ ገንዘብ ወይም ቁም ከብት፡ ካሳ (2)
5. የዮፍታሔ ንጉሤ ግጥም(7)
12. ኢዮሐ አበባዬ(5)
13. በፊት(3)
30. በምስር ወይም በሩዝ ሊሠራ የሚችል ምግብ(4)

ወደታች

22. ለፊሳም ይሆናል(3)
24. አዲስ የግዕዘል ፈጠነ መጽሐፍ ስም(5)
25. አቶ አልአዛር፡ አቶ አ፡ አሌ ስምንተኛው ጋጋታ (5)

ማስታወሻ!

የእንቆቅልሽ መልስ በቀጣይ ዕትም የሚወጣ ሲሆን ፡ ሙከራችኹን በቴሌግራም፡ ፌሰቡክ እና ኢንስታግራም አድራሻችን አጋሩን።

መዲና ቅጽ 1 ቁጥር 1 ይህችን ትመስል ነበር።

ሀሳብ አስተያየት ካላችኹ በmedinadigitalmagazine@gmail.com ቢልኩልን ለቀጣይ ዕትም እናርማለን።

በወደዱት አምድ ላይ ያዘጋጁት ጽሑፍ ካለ ለመላክ አያመንቱ። አድራሻ medinadigitalmagazine@gmail.com

መዲና መጽሔትን በሁሉም ሶሻል ሚድያዎች ላይ ይወዳጁ!

Medina መዲና

Medina መዲና

@Medinamagazine